# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 186 መጋቢት 6 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia




## “ማዕከሉ እንደሀገር ያለውን የስክነትና አርቆ የመመልከት ስብራት ለመጠገን ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል”

### - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- “ለነገዋ” የሴቶች ተሐድሶና ክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል እንደሀገር ያለውን የስክነትና አርቆ የመመልከት ስብራት ለመጠገን ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ።

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የተገነባውን “ለነገዋ” የሴቶች የተሐድሶና የክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸውና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ በተገኙበት ትናንትና ተመርቋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በማበልጸጊያ ማዕከሉ የምረቃ መርሐ ግብር ባደረጉት ንግግር እንዳስታወቁት፣ በአዲስ አበባ ከተገነቡ ፕሮጀክቶች ሁሉ ድንቅ ሥራ የሆነው የማበልጸጊያ ማዕከሉ የኢትዮጵን ስብራት ለመጠገን ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል።

ልጆች ተንከባክበን በማስተማር ለወግ ለማዕረግ ማብቃት ሲገባን ባሉብን ዘርፈ ብዙ ድካሞች ለጎዳናና ላልተገባ የሕይወት መስመር ይዳረጋሉ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ የነዚህን ዜጎች የሕይወት መስመር ማቅናት እንደሀገር

“ማዕከሉ እንደሀገር ያለውን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## “የመደመር ትውልድ” መጽሐፍ በድምፅ ትረካ ተዘጋጅቶ ቀረበ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) “የመደመር ትውልድ” መጽሐፍ በድምጽ ትረካ ተዘጋጅቶ ቀረበ።

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) “የመደመር ትውልድ” መጽሐፍ የድምፅ ትረካ በአዲስ ዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት ተዘጋጅቶ በትላንትናው ዕለት በዓድዋ ድል መታሰቢያ ተመርቋል።

የአዲስ ዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መሐመድ ሀሰን በአዲስ ዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት በድምፅ የተተረከው “የመደመር ትውልድ” ከትረካው ባሻገር በርካታ የቪዲዮ ጥቅሎችን መያዙን ገልጸዋል።

የመጽሐፉ ኦዲዮቪዥዋል ሕዝቡ በተለያዩ አማራጮች እንዲያገኘው ታስቦ እንደተዘጋጀም ተናግረው፣ መጽሐፉ ከያዘው ጥልቅ ይዘት አንጻር በትረካ መቅረቡ ተደራሽነቱን እንደሚያሰፋው አስረድተዋል።

“የመደመር ትውልድ” ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አቶ አህመድ ሽዴ

## ሀገር በቀል

### የኢኮኖሚ ሪፎርሙ በችግሮች ውስጥም አመርቂ ውጤቶችን አስመዝግቧል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዓመታት ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ጫና ቢያሳድሩም በተከናወኑ ጥረቶች ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርሙ አመርቂ ውጤቶችን እንዳስመዘገበ

ሀገር በቀል... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## የሀገር መከላከያ ሠራዊት የሠላም አስከባሪ “ሞተራይዝድ” ሻለቆችን አስመረቀ

**ተስፋ ፈሩ**

ሁርሶ፡- በሀገር መከላከያ ሠራዊት የሠላም ማስከበር ማዕከል የሁርሶ ኮንቲንጀት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ያሠለጠናቸውን የሠላም አስከባሪ ሞተራይዝድ ሻለቆች ትናንት አስመረቀ።

የተመረቁት የ18ኛና 19ኛ ሻለቆች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥላ ስር በጎረቤት ሀገር ደቡብ ሱዳን ጁባ የሚሠማሩ መሆናቸው ተገልጿል።

የመከላከያ ጤና ዋና መምሪያ ኃላፊ ሌተናል ጄኔራል ጥጋቡ ይልማ በምረቃ ሥነሥርዓቱ ላይ ባደረጉት ንግግር፣ ምርቃቱ የጥቁር ሕዝቦች አኩሪ ድል በሆነው የዓድዋ ድል በተከበረ ማግስት መከናወኑ ልዩ እንደሚያደርገው ገልፀዋል።

ለተመራቂዎቹ ባደረጉት የመመሪያ ንግግርም የሀገራችንና የተቋማችን ወታደራዊ ዲፕሎማት ሆናችሁ የሚያኮራ ታሪክ ለመፈጸም ሥልጠናችሁን በጀግንነት ያጠናቀቃችሁ ሠልጣኞች፣ ስኬታማ ተልዕኮ ፈጽማችሁ በመመለስ የኢትዮጵያን ስም በማስጠራት ሠራዊታችን በዓለም ላይ የምንጊዜም ተመራጭ ሆኖ እንዲቀጥል

የሀገር መከላከያ ሠራዊት... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ፎቶ፡- በረሀኑ ታደሰ









ማርታ ማሙዬ

# የወጣቶች
## የሥነ-ተዋልዶ ጤና ልዩ ትኩረት ያስፈልገዋል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በወጣቶች የሥነ-ተዋልዶ ጤና ጉዳይ በተለያዩ መስኮች ልዩ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ሀገር አቀፍ ወጣት ሴቶች በጎ አድራጎት ድርጅት አስታወቀ፡፡

በወጣቶች ሥነ-ተዋልዶ ጤና ላይ ያተኮረ ውይይት ትናንትና በተካሄደበት ወቅት ሀገር አቀፍ ወጣት ሴቶች በጎ አድራጎት ደርጅት መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ማርታ ማሙዬ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ የወጣቶች የሥነ-ተዋልዶ ጤና ጉዳይ ላይ ሰፊ ክፍተቶች ያሉ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ወጣቱ የኅብረተሰብ ክፍል ስለ ሥነ-ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑ ለተለያዩ ችግሮች እየተጋለጠ ነው ያሉት ሥራ አስኪያጇ፤ በተለይም በትምህርት ቤቶች የሚገኙ ወጣቶች በግንዛቤ እጥረት ምክንያት ላልተፈለገ እርግዝና ፣ ውርጃ፣ እንዲሁም ለተለያዩ በሽታዎች እየተጋለጡ መሆኑን አንስተዋል፡፡

እንደ ሀገር ችግር በሰፊው እንዳለ የሚታወቅ ቢሆንም በቂ ትኩረት ካለማግኘቱ የተነሳ የወጣቶች የሥነ-ተዋልዶ ጤና ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የሥነ-ተዋልዶ ጤና ሁለቱንም ፆታዎች የሚመለከት አጀንዳ ቢሆንም ሴቷን የበለጠ ተጎጂ የሚያደርጓት ምክንያቶች በመኖራቸው በተለያዩ መስኮች የሚሠሩ ተቋማት በጉዳዩ ላይ ሰፊ ትኩረት ሰጥተው ሊሠሩ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የኔትዎርክ ኦፍ ኢትዮጵያን ውመን አሶሴሽን ፕሮግራም ማናጀር ሚስጥረ አለባቸው በበኩላቸው የሥነ ተዋልዶ ጤና ጉዳይ ሁሉንም ሰው ያካተተ ቢሆንም በዋናነት ወጣት ሴቶችን ይመለከታል ብለዋል ፡፡

በኢትዮጵያ የሥነ-ተዋልዶ ጤና ላይ ሰፊ የግንዛቤ ችግር እንዳለ ገልጸው፤ በተለይም ወጣት ሴቶች ከፍተኛ ችግር እንደሚያጋጥማቸው ተናግረዋል፡፡

በተለያዩ ጊዜያት ወጣቶች ወደ ፆታዊ ግንኙነት ሲገቡ ምን ጉዳዮች ላይ መጠንቀቅ እንዳለባቸው ሳያውቁና መረጃ ሳይኖራቸው በስሜታዊነት ይጎዳሉ ያሉት ሚስጥረ፤ በዚህ ምክንያት ሴቶች በሕይወታቸውን ሙሉ ለሚከተላቸው ችግር እየተጋለጡ መሆኑን አንስተዋል።

ወጣቶች ያለ ዕድሜያቸው ወሲባዊ ግንኙነት በመጀመራቸው ለተለያዩ በሽታዎች የመጋለጥና ከዓላማቸው እየተሰናከሉ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

መንግሥት በጉዳዩ ላይ ትኩረት በመስጠትና ወጣቱን ያማከለ ሥራዎች በመሥራት፣ ወጣቶች ላይ የሚሠሩ ተቋማት እርስ በርስ ትስስር በመፍጠር ውይይቶችን ማካሄድ እንዲሁም ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በማከናወን ችግሩን መቅረፍ እንደሚገባቸውን አመላክተዋል።

# በሸማቾች ላይ የሚደርሰውን የመብት ጥሰት ለመከላከል በትብብር መሥራት ያስፈልጋል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ሸማቾች በግብይት ሥርዓቱ የሚደርስባቸውን የመብት ጥሰት ለመከላከል በትብብር መሥራት እንደሚገባ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በዓለም ለ41ኛ በኢትዮጵያ ለ11ኛ ጊዜ የተዘጋጀውን የሸማቾችን ቀንን "በኅብር መብታችንን እናስከብር" በሚል መሪ ሀሳብ ከባለድርሻ አካላት ጋር ትናንትና አክብሯል።

በሚኒስቴሩ የሀገር ውስጥ ንግድ ሸማቶች ጥበቃ መሪ ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሮ መስከረም ባሕሩ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ሸማቾች በግብይት ሥርዓት ላይ እየደረሰባቸው ያለውን የመብት ጥሰት ለመከላከልና በቅንጅት መሥራት ይገባል።

ማኅበረሰቡ ገዝቶ በሚጠቀመው ምርት የጤና ችግር እንዳይደርስበት የመጠበቅ ሥራ እየተሠራ መሆኑን አመላክተው፤ በንግድ ሥርዓት ውስጥ ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ሸማች በመሆኑ በሚገዛው ምርት ጤንነቱ የተጠበቀ፤ ስለምርቱ በቂ መረጃ ያለው፤ የመምረጥ መብቱ የተከበረ፣ የመደመጥና ያለመግዛት መብቱ በሰፊው እንዲከበር መሥራት ይገባል ብለዋል።

ሸማች በሀገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ትልቅ ሚና ያላቸው በመሆኑ በግብይት ሂደት ላይ በሕግ የተቀመጠለት መብት ሊከበርለት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ሸማቶች አንድ ምርት ገዝተው በመጠቀም የደረሰባቸው ጉዳት ካለ የመካስ መብት አላቸው ያሉት ወይዘሮ መስከረም፤ ሸማቹ ማኅበረሰብ መብቶቹን አውቆ ለሚደርስበት የመብት ጥሰት ጥብቅና መቆም እንዳለበት አመላክተዋል።



ወይዘሮ መስከረም ባሕሩ

በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሸማቶች መብት ጥበቃና ግንዛቤ ዴስክ ኃላፊ አቶ ሰይፉ አየለ በበኩላቸው፤ ነጋዴው ማኅበረሰቡን እንዲያገለግል፣ ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ እንዲያደርግ፣ ገበያውን የሚመጥን ምርት እንዲያቀርብ የሚያስገድድ ሕግ መኖሩን ተናግረዋል።

ነጋዴው ለሚሸጠው ምርት ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ሲኖርበት ሸማቹ ደግሞ ለገዛው ምርት ደረሰኝ የማግኘት መብት እንዳለው ማወቅ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ጊዜያቸው ያለፉባቸው ምርቶች ለገበያ ቀርበው በሸማቹ ላይ ጉዳት እንዳይደርሱ፤ በሀገር ውስጥ የሚመረቱና ከውጪ የሚገቡ ምርቶች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ሰይፉ፤ በሸማቶች ላይ እየደረሰ ያለውን የመብት ጥሰት ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሠራት እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

በሀገሪቱ እየተስፋፋ ያለውን የንግድ እንቅስቃሴ ተከትሎ በገበያ ላይ የሸማቾችን ጤንነትና ደህንነት የሚጎዱ ተግባራት እንዳይፈጠሩ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የፀረ ውድድርና የሕግ ጥሰት መከላከል ዴስክ ኃላፊ አቶ ጌትነት አሸናፊ ተናግረዋል።

ከባዕድ ነገሮች ጋር የተቀላቀሉ፤ የአገልግሎት ዘመን ያለፈባቸው፤ ደረጃቸውን ያልጠበቁና የአገልግሎት ጊዜያቸው አልፎ እንደ አዲስ ለገበያ እንዲውሉ የሚደረጉ ምርቶች አሉ፤ ምርቶች ገበያ ላይ ውለው የማኅበረሰቡ ጤና ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ የመከታተልና የመቆጣጠር ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮና የሸማቾች መብት ጥሰት ጥበቃ ማኅበር፣ ከፌዴራል ወንጀል ምርመራ ቢሮ ጋር የሸማቾች መብት በተመለከተ ውይይት በማድረግ የሸማቾችን ቀንን አክብሯል።



# በኢትዮጵያ ዝቅተኛ የሆነውን የሴቶች የፋይናንስ አካታችነት ማሳደግ ይገባል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ ፡- በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሻለ ቢሆንም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት ዝቅተኛ የሆነውን የሴቶች የፋይናንስ ዘርፍ አካታችነት ማሳደግ እንደሚገባ ጥናቶቹ አመላከቱ።

ፋይናንሻል ሴክተር ዴፕኒንግ ኢትዮጵያ (FSD Ethiopia) የተሰኘው ተቋም በአፍሪካ የሴቶች የፋይናንስ አቅምን በማሳደግ ሂደት የሚያጋጥሙ መሰናክሎችና ዕድሎች ላይ ያተኮሩ ሁለት ጥናቶችን አቅርቦ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ትናንትና ውይይት አካሂዷል።

በተቋሙ የፋይናንስ አካታችነት ዳይሬክተር አቤል ታደለ በመድረኩ እንደገለጹት፤ የዓለም ባንክ በየሁለት ዓመቱ የሚያወጣውን መረጃ መሠረት በማድረግ የሴቶች የፋይናንስ አካታችነት እንዳያድግ ችግር የሆኑ ጉዳዮች ምን እንደሆኑ የሚለዩ ሁለት ጥናቶችን ተዘጋጅተዋል።

ጥናቶቹ በዓለም አቀፍ ደረጃ እያደገ ቢመጣም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት ዝቅተኛ የሆነውን የሴቶች የፋይናንስ ዘርፍ አካታችነት ማሳደግ እንደሚገባ ማመላከታቸውን አስረድተዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሴቶች የፋይናንስ አካታችነት እያደገ ቢመጣም ኢትዮጵያን ጨምሮ እንደ ናይጄሪያ፣ ታንዛኒያ፣ ኬንያ እንዲሁም ዑጋንዳ ባሉ ሃገራት አካታችነቱ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

በገጠርና በከተሞች ለሴቶች ምቹ የሆኑ የፋይናንስ አካታችነት ሥርዓቶችን አለመስፋፋታቸው ሴቶች የፋይናንስ አቅማቸው እንዳያጎለብቱና ውሳኔ ሰጪ እንዳይሆኑ ትልቅ ተግዳሮት መፍጠሩን ገልጸዋል።

በተለይ በኢትዮጵያ ሴቶች የፋይናንስ አቅማቸው ከፍ እንዳይል የባንኮችና ብድር የሚያቀርቡ ተቋማት ውስንነት ዋነኛው ተግዳሮት መሆኑ በጥናቱ መጠቆሙን አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ ልክ እንደሌሎች ታዳጊ ሀገራት በፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነትና አጠቃቀም ላይ ያለውን የሥርዓተ-ፆታ ክፍተት ለመቅረፍ አሁንም ብዙ ሥራ ይጠበቅባታል ብለዋል።

የሴቶችን የፋይናንስ አካታችነትን ለማሳደግ በዲጂታል ሥርዓት መጠቀም ዋነኛው መፍትሔ መሆኑን ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል።

በዓለም ባንክ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ መሠረት የሴቶች ዲጂታል የፋይናንስ ተጠቃሚነት ለማሳደግና ኢኮኖሚው ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪ እንዲሆኑ ለማስቻል ሰፊ ሥራ መከናወን እንዳለበት አንስተዋል።

የዲጂታል የፋይናንስ አካታችነት ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ ቀላል ቢሆንም ሃገሪቱ ላይ ካለው አስቻይ ሁኔታ አንጻር ተደራሽነቱን ማረጋገጥ ላይ ከፍተኛ ሥራ ይጠይቃል ሲሉ ገልጸዋል ።

በመድረኩ የፖሊሲ አውጪዎች፣ ምሁራን፣ የፋይናንስ ተቋማት ኃላፊዎች፣ የልማት ድርጅቶችና በቴክኖሎጂ ላይ የተሠማሩ ኩባንያ ተወካዮች ተገኝተዋል።

# የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ በውሃና ኢነርጂ መስክ
## የአመራር ልማትን ማጠናከር ያስፈልጋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡-የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ በውሃና ኢነርጂ መስክ የአመራር ልማትን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት ትላንት ተፈራርመዋል።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ በስምምነቱ ወቅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ በውሃና ኢነርጂ መስክ የአመራር ልማትን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

በዘርፉ የሚከናወኑ አቅም ግንባታ ሥራዎችን መነሻ በማድረግ ከልህቀት አካዳሚው ጋር የመግባቢያ ሰነድ መፈረሙንም አመላክተዋል።

ተቋሙን በሰው ኃይል፣ የውሃ ሀብት አስተዳደር፣ በመጠጥ ውሃ፣ በአስተዳደርና ተመሳሳይ ጉዳዮች አቅምን መገንባት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ከዓለም ባንክ ከሚገኙ ድጋፎች ከኢትዮጵያ ውጪ በተለያዩ ሀገራት ላይ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች እንደሚደረጉ ጠቅሰው፤ የመግባቢያ ስምምነቱ ተቋሙ ለሥልጠናዎች የሚያወጣውን የውጪ ምንዛሪ እንደሚያስቀር ገልጸዋል።

አካዳሚው ተቋማትንና ሀገርን ለመገንባት የሚያስችል መሆኑን ገለጹት ኢንጂነር ሀብታሙ በቀጣይ የጋራ እቅድን በማውጣትና የሚሰጡ ሥልጠናዎችን በመለየት ሀገሪቱን የውሃ ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም መነሻ እንደሚሆን አስረድተዋል።

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ርዕሰ አካዳሚ አቶ ዛዲግ አብረሃ በበኩላቸው፤ በውሃና ኢነርጂ መስክ የሚከናወነው የአመራር ልማት ሥራ በቀጣይ ለአፍሪካ ሀገራትም እንዲተርፍ ይደረጋል ሲሉ አመላክተዋል።

በአሁኑ ወቅተ በዘርፉ የሥልጠና እንጂ የአመራር ልማት ፕሮግራሞች አለመኖራቸውን ጠቅሰው፤ ሀገሪቱ በበርካታ መስኮች የአመራር ልማት መስኮች እንደሚያስፈልጋት ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የውሃ ልማትና ሀብቷን እንድትጠቀም የሚያስችል አመራር መፍጠር ያስፈልጋል ያሉት ርዕሰ አካዳሚው፤ በውሃ ሀብት ልማት ዘርፍ የሚፈጠር አመራር የኢትዮጵያን ዕጣ ፋንታ ይወስናል ብለዋል፡፡

የውሃው ሀብት ከፍተኛ የመሪነትና ቦታና ሥራ የሚያስፈልገው ዘርፍ መሆኑን ገልጸው፤ ኢትዮጵያ የውሃና ኢነርጂ ሀብቷን በተጠቀመች ቁጥር መዳረሻዋ ብልጽግና ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

አቅም ግንባታው ቀደም ሲል ወደ ይወጣ የነበረው የውጪ ምንዛሪ በሀገር ውስጥ ለማስቀረት እንደሚያስችል የጠቆሙት አቶ ዛዲግ፤ በዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ የአመራር ልማት ፕሮግራም አመራሮች ተደግፎ ወደ ፊት ለማራመድ ያስችላል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለአፍሪካ የሚተርፍ የአመራር ልማት ሥራዎችን እንደምትሰራ ጠቅሰው፤ በውሃና ኢነርጂ መስክ የሚሠራውን የአመራር ልማት ሥራ በቀጣይ በዘርፉ የተሻለ ውጤት እንደሚያመጣ እምነታቸው መሆኑን ገልጸዋል።



ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ እና አቶ ዛዲግ አብርሃ

# ኮንትሮባንድ ሕጋዊ ለሆነው የንግድ
## ሥርዓት ፈተና ሆኖ ቀጥሏል

**ፍሬሕይወት አወቀ**

አዲስ አበባ፡- የኮንትሮባንድ ንግድ ሕጋዊ ለሆነው የንግድ ሥርዓት ፈተና ሆኖ መቀጠሉን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ ገብረመስቀል ጫላ በዘርፉ እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎችን አስመልክተው ከትናንት በስቲያ ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደገለጹት፤ ኮንትሮባንድ ንግድ በሀገሪቷ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑን ገልጸዋል።

ኮንትሮባንድ ንግድ በተለይም በሀገሪቱ ወጪ ምርቶች ላይ ማለትም በማዕድን፣ በጫት፣ በቁም እንስሳት፣ በጥራጥሬና በቅባት እህሎች ወጪ ንግድ ላይ ከፍተኛ ጫና በማሳደር ሀገሪቷ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ እያሳጣት ነው ብለዋል።

ኮንትሮባንድ ንግድ ሕገወጥ ነጋዴው የበለጠ አተርፋለሁ በሚል የሚበለጽግበት መሆኑን ጠቅሰው፤ ሀገር ውስጥ መግባት ያለበትን የውጭ ምንዛሪ ውጭ ሀገር ለማስቀረት እጅግ በተጠናና በተቀናጀ መንገድ የሚሠራ ከባድ ፈተና ሆኖ መቀጠሉን አመላክተዋል።

ኮንትሮባንድ ዕቃ የያዘ መኪና በቁጥጥር ስር ቢውል ባለመኪናው መኪናውን ዞር ብሎ አይመለከትም ወይም አይፈልገውም ያሉት አቶ ገብረመስቀል፤ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ባለንብረቱ ቀደም ሲል ከኮንትሮባንድ ንግዱ ያገኘው ትርፍ ከመኪናው ዋጋ በላይ በብዙ እጥፍ ስለሚሆን ነው ሲሉ አስረድተዋል። ስለዚህ ኮንትሮባንድ የንግድ ሥርዓቱ ችግር ብቻ ሳይሆን ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትም እንቅፋት የሆነ ቁልፍ ችግር ነው ብለዋል።

ኮንትሮባንድ በወጪ ንግድም ሆነ በገቢ ንግድ በስፋት የሚታይና የማይነካካው ዘርፍ እንደሌለ የገለጹት አቶ ገብረመስቀል፤ ይህም አጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ መሆኑን አመላክተዋል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርም ይህን ለመቆጣጠር ከፍተኛ የሆነ እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑን ገልጸው፤ በተለይም በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራ የኮንትሮባንድ ቁጥጥር ግብረኃይል ኮሚቴ መቋቋሙን ተናግረዋል።

የተቋቋመው ግብረኃይልም በየጊዜው



አቶ ገብረመስቀል ጫላ

እየገመገመና አቅጣጫ እያስቀመጠ መሆኑን ጠቅሰው፤ የፀጥታ መዋቅሩን፣ የፌዴራልና የክልል ፖሊስን እንዲሁም የጉምሩክ መዋቅርን ጭምር እያጠናከረ መሆኑን ገልጸዋል። ወደፊትም ድንበርን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍና በማጠናከር ኮንትሮባንድ ንግድን ደረጃ በደረጃ መቀነስ የሚቻል እንደሆነ አመላክተዋል።

በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ረጅም ድንበር ባለው ሀገር ኮንትሮባንድን መቀነስ እንጂ ዜሮ ማድረግ አይቻልም ያሉት አቶ ገብረመስቀል፤ የኮንትሮባንድ ንግድን ለመቀነስ ድንበርን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መደገፍ አንዱ መፍትሔ ሲሆን፤ ከዚህ ባሻገርም ኢትዮጵያ አሁን ላይ እየተቀላቀለች ያለው የንግድ ሥርዓት ማለትም ነፃ የንግድ ቀጣና ኮንትሮባንድን ለመከላከል ሁነኛ መፍትሔ እንደሚሆን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ እየተቀላቀለች ያለው ነፃ የንግድ ቀጣና ወጪም ሆነ ገቢ ምርት ሥርዓት ባለው መንገድ ተመዝግቦ የሚወጣና የሚገባ በመሆኑ ከዚህ ውጭ ያለው ምርት በሙሉ ተቀባዩን ሀገር ጭምር ችግር ውስጥ የሚከት መሆኑን የገለጹት አቶ ገብረመስቀል፤ ለዚህም ነፃ የንግድ ቀጣናው ኮንትሮባንድ ንግድን በእጅጉ እንዲቀንስ የሚያደርግና በብዙ የሚያግዝ እንደሆነ ነው ያመላከቱት።

# ምክር ቤቱ የአቶ ክርስቲያን ታደለን
## ያለመከሰስ መብት አነሳ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትን በኃይል ለመናድ በመንቀሳቀስ ተጠርጥረዋል ያላቸውን የአቶ ክርስቲያን ታደለን ያለመከሰስ መብት አነሳ። ምክር ቤቱ የተጓደሉ የአማካሪ ኮሚቴ አባላትን እና የቋሚ ኮሚቴ አመራሮችን ለማሟላት የቀረቡትን የውሳኔ ሀሳቦች መርምሮ አጽድቋል።

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን በ17ኛ መደበኛ ስብሰባው የአቶ ክርስቲያን ታደለን ያለመከሰስ መብት በውሳኔ ቁጥር 9/2016 በአብላጫ ድምጽ አፅድቋል።

የአቶ ክርስቲያን ታደለ ያለመከሰስ መብትን አስመልክቶ ለምክር ቤቱ ማብራሪያ ያቀረቡት የፍትሕ ሚኒስትር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶ/ር)፤ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል ምርመራ ቢሮ በተጠርጣሪውና አባሪዎቹ ላይ የወንጀል ምርመራ መዝገብ በማደራጀት ምርመራ አከናውኖ መዝገቡን መላኩን ገልጸዋል።

በምርመራ መዝገቡ የተካተቱ የሰው፣ የሰነድና የቴክኒክ ማስረጃዎችን በማገናዘብ ምርመራ መደረጉን ጠቁመው፤ መዝገቡ ተጠርጣሪው በአማራ ክልል ተደራጅቶ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትን በኃይል ለመናድ ከሚንቀሳቀስ የፀረ ሠላም ኃይል ጋር ትስስር ያለውና ለዚህ ቡድንም መመሪያ የሚሰጥ መሆኑንም ከመዝገቡ መረዳት መቻሉን አመላክተዋል።

ተጠርጣሪው ፀረ-ሠላም ኃይል በማደራጀት በሀገር መከላከያ ሠራዊት ላይ ጥቃት እንዲሰነዘር ትእዛዝ ሲሰጡ እንደነበር ማስረጃዎቹ እንደሚያስረዱም በማብራሪያቸው አንስተዋል።

የተጠርጣሪው ድርጊት የሽብር አዋጅን ለመከላከል በወጣው አዋጅ ቁጥር 1176/2012 አንቀጽ 3 እና ተከታዮቹ እንዲሁም በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 238 እና ተከታዩቹ ስር የሚያስከስስ ከባድ ወንጀል መሆኑንም ጠቁመዋል።

በተጠርጣሪው ላይ በፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ እንዲቻል የተጠርጣሪው ያለመከሰስ መብት በሕገ መንግሥቱ 54 ንዑስ አንቀጽ 6 እና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአሠራርና የሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 አንቀጽ 115 መሠረት እንዲነሳ ሲሉ ጠይቀዋል።

አቶ አበባው ደሳለው በበኩላቸው፤ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ትግበራ ወቅት ማሰር በጣም ቀላል ነው፤ በፖለቲካ ልዩነት ማንኛውንም ሰው እየወሰዱ ማሰር ያለውን ችግር ያወሳስበዋል ብለዋል።

ያለመከሰስ መብቱ ሳይነሳ ስምንት ወር ያክል አስሮ ማቆየቱም ትክክል አይደለም፣ የሚያዋጣው ፖለቲካዊ መፍትሔና ድርድር ነው ሲሉም አንስተዋል።

በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ትግበራ ወቅት ሕግ አውጭውም የዳኝነት አካሉም ምንም ሚና የላቸውም፤ ያለመከሰስ መብቱ አሁን የሚነሳበት ሂደትም ግልጽ አይደለም በማለት የቀረበውን ሃሳብ ተቃውመዋል።

አቶ ኢሳ ቦሩ በበኩላቸው፤ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚታወጀው የሃገርን ደህንነት፣ ሠላምና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለማስጠበቅ መሆኑን አስታውሰዋል። የውሳኔ ሃሳቡን ተቀብለን ብናፀድቅ የተሻለ ነው ሲሉ የድጋፍ ሃሳብ አንስተዋል።

ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶ/ር)፤ ተፈጻሚነቱ ተገድቦ ምክር ቤቱን ፍቃድ መጠየቅ ሳያስፈልግ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማዕቀፍ ውስጥ በቁጥጥር ስር ማዋል እንደሚቻል አስታውሰዋል።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚጣለው ተጠርጥረው በሚያዙ ሰዎች ላይ በ48 ሰዓታት ፍርድ ቤት አልቀረብኩምና በነፃ መለቀቅ አለባቸው የሚል ጥያቄ እንዳይነሳ ለማድረግ መሆኑን አስረድተው፤ ሕግ አስፈጻሚው በመደበኛው ሥርዓት እንዲታይ ለማቅረብ ከፈቀደ ጉዳዩን ማቅረብ የሚችልበት አግባብ እንዳለ ተናግረዋል።

ነገር ግን በመደበኛው ሥርዓት ቢታይ ተጠርጣሪዎች ራሳቸውን እንዲከላከሉ ስለሚያስችልና ፍትሐዊ በሆነ ሂደት እንዲያልፉ ሲባል ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት መውሰድ የተሻለ መሆኑን አቋም መያዙን አንስተዋል።

በመጨረሻም ምክር ቤት የአቶ ክርስቲያን ታደለን ያለመከሰስ መብት በውሳኔ ቁጥር 9/2016 በአብላጫ ድምጽ አፅድቋል።

በተጨማሪም ምክር ቤቱ በተለያዩ ምክንያቶች የተጓደሉ የአማካሪ ኮሚቴ አባላትንና የቋሚ ኮሚቴ አመራሮችን ለማሟላት የቀረበውን የውሳኔ ሃሳቦችን መርምሮ አፅድቋል። የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ዕጩ ምክትል ዕንባ ጠባቂ አቅራቢ ኮሚቴ ለማቋቋም የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ አፅድቋል።

በሌላ በኩል ምክር ቤቱ በትናንት ውሎው በኢትዮጵያ እና በጆርዳን መንግሥታት መካከል በሥራ ስምሪት ዘርፍ የተፈረመ የመግባቢያ ሰነድ ረቂቅ አዋጅ በሙሉ ድምፅ አጽድቋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች የሚደነቁ ናቸው!

ሴቶች በሁሉም ማኅበረሰብ ሊባል በሚችል ደረጃ ለዘመናት አድሏዊ ልዩነት እየተደረገባቸው እና ሰብዓዊ መብቶቻቸው ሳይከበሩላቸው መቆየታቸውን ከታሪክ መመልከት እንችላለን። እነዚህን የመብት አለመከበር እና ፆታን መሠረት ያደረጉ ልዩነቶችን ለማስወገድ በርካታ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና ሀገር አቀፍ ሕጎች ቢኖሩም የሴቶችን መብቶች ሙሉ ለሙሉ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

እስከዛሬ በሴቶች እኩል ተጠቃሚነት ዙሪያ በተሠሩ ሥራዎች የተነሳ ጉልህ ለውጦች ቢኖሩም አሁንም ሙሉ በሙሉ የፆታ እኩልነትን ለማስመዝገብ ትልቅ ትግል የሚጠይቅ ጉዳይ ሆኖ በመቀጠል ላይ ነው። ሴቶች በተለያዩ የዓለም ሀገራት መድልዎ፣ ጥቃት፣ የትምህርትና የጤና አጠባበቅ ተደራሽነት ውስንነት እንዲሁም የኢኮኖሚ ልዩነቶች ይደርስባቸዋል።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በሴቶች እና በወንዶች ያለው የኢኮኖሚ ልዩነት ስንመለከት፤ ሴቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ በአማካይ ከወንዶች በ23 በመቶ ያነሰ ገቢ ያገኛሉ። የሴቶች በአመራር ቦታዎች ላይ ያላቸው ውክልናም ዝቅተኛ ነው፡፡ በፓርላማ ውስጥም መቀመጫ ማግኘት የቻሉት 24 በመቶ የሚሆኑ ሴቶች ብቻ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያም ያለው ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል የሚታይበት ቢሆንም አሁንም በርካታ ቀሪ የቤት ሥራዎች እንዳሉት እሙን ነው፡፡ ሆኖም ኢትዮጵያ የሴቶችን ጉዳይ ሕገ መንግሥታዊ ዕውቅናና ከለላ እንዲኖረው በማድረግ ጭምር በከተማና በገጠር የሚኖሩ ሴቶች መብታቸው ተረጋግጦላቸው እንዲኖሩ ለማድረግ በርካታ ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው፡፡

በተለይም ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ የሴቶችን ማኅበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው፡፡ መንግሥት እንደ አዲስ ባዋቀረው ካቢኔ ውስጥ 50 በመቶውን ሴቶችን እንዲይዙ በማድረግ የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ በማሳደግ ረገድ አርዓያነት ያለው ተግባር ማከናወን ተችሏል፡፡

የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግ የተሠራውም ሥራ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ ከጤና ጋር በተያያዘም «አንድም ሴት በወሊድ የተነሳ አትሞትም» በሚል ሴቶች የተሻለ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ የጤና ተቋማትን ከማስፋፋት ጀምሮ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ አቅምም ለማሳደግም መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

ትናንት ለምረቃ የበቃው የሴቶች የተሐድሶና የክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል የዚሁ ጥረት አንዱ ማሳያ ነው፡፡ ማዕከሉ በዋነኛነት በወሲብ ንግድ ላይ የተሠማሩ ሴቶችን በመቀበል ሙያዊ እና ሥነ ልቦናዊ ድጋፍ፣ ክትትልና ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ በማድረግ ወደ ሥራ እንዲሠማሩ የሚያስችል ሲሆን በአንድ ዙር ብቻም 10 ሺህ ሴቶችን ተቀብሎ የማሠልጠን አቅም ያለው ነው፡፡ “ለነገዋ” በሚል የተሰየመው ይኸው የሴቶች ተሐድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል የሴቶችን እኩልነትና ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የላቀ ሚና ይኖረዋል፡፡

ሴቶች በማዕከሉ ቆይታቸው ከሚያገኙት የሥነ ልቦና ድጋፍ በተጨማሪ በሥነ-ውበት፣ በከተማ ግብርና፣ በምግብ ዝግጅት፣ በከተማ ውበት አጠባበቅና በኮምፒዩተር ሙያ ሥልጠና በመውሰድ ወደ ሥራ እንዲገቡም ዕድል ይፈጥራል፡፡ ማዕከሉ በውስጡ የተሐድሶ ሥልጠና የሚሰጥባቸው የክህሎት ማበልፀጊያ፣ የማሰልጠኛ ማዕከላት፣ የሥነ-ልቦና እና ምክር አገልግሎትንም ያቀፈ ነው፡፡

ይህ ማዕከልም መንግሥት የሴቶችን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እያከናወናቸው ካሉ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች አንዱ ማሳያ ነው፡፡ የሴቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ ጾታ ተኮር የሆኑ ፖሊሲዎች መተግበር አለባቸው፤ ከእነዚህም መካከል ሴቶች እኩል ክፍያ፣ ብድር የማግኘት ዕድል እና የሥራ ፈጠራ ድጋፎችን እንዲሁ ሊያገኙ ይገባል። የግል ሴክተሩም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን እንዲያበረታታ እና አድሎአዊ ድርጊቶችን እንዲያስወግድ ማበረታታት አስፈላጊ ነው።

ሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ የተለያዩ መሻሻሎች ቢታዩም አሁንም የተለያዩ ክፍተቶች አሉ፡፡ እነዚህን ክፍተቶች ለማጥበብም የሕግ ማሻሻያዎችን መተግበር፣ የትምህርት እና ግንዛቤን ማስበጫዎችን ማድረግ፣ ሴቶችን በኢኮኖሚ በማብቃት፣ ጤናን እና ደኅንነትን በማረጋገጥ እና ዓለም አቀፍ ትብብርን በማጎልበት የሴቶችን እኩል ተጠቃሚነትን ለማምጣት መሠራት አለበት፡፡ እያንዳንዷ ሴት መብቷን የምትጠቀምበት እና አቅሟን የምታሳይበት ማኅበረሰብ እንዲፈጠር ግለሰቦች፣ ማኅበረሰቦች እና መንግሥታት በጋራ መትጋት ይገባል!


**አዲስ ዘመን**

እፕድ ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከዓባይ ግድብ 13ኛ ዓመት ባሻገር፤

(ክፍል አንድ)

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ አፈፃፀም 95 በመቶ፣ የግድቡ አጠቃላይ የሲቪል ሥራው ግንባታ ደረጃ ደግሞ 98 ነጥብ 9 በመቶ የደረሰ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ከታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ በሁለት ተርባይኖች 540 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል እያመነጨ ይገኛል።

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት የሕዝብ ግንኙነት ዋና ዳይሬክተር አቶ ኃይሉ አብርሃም ሰሞኑን እንደገለፁት፣ ግድቡ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ የሚያመርተው ኤሌክትሪክ ኃይል 5ሺ150 ሜጋ ዋት ይደርሳል፡፡ አሁን ላይ ግድቡ የያዘው የውሃ መጠን 42 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ሲሆን ሲጠናቀቅ ፤ የሚይዘው ውሃ መጠን ወደ 74 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ከፍ ይላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በ2016 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ውስጥ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ከ643 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡም ተገልጿል። በዚህም የግድቡ ግንባታ ከተጀመረበት 2003 አንስቶ እስከ ታኅሣሥ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ከሀገር ውስጥ፣ ከውጪ እና ከቦንድ ሽያጭ ልገሳ እና ከልዩ ልዩ ገቢዎች ወደ 19 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ሃብት መሰብሰቡንም ነው አቶ ኃይሉ ገልጸዋል፡፡

በዚህ መልኩ ከፍ ያለ ሕዝባዊ ተሳትፎም፣ የግንባታ አፈጻጸምም የታየበት የዓባይ ግድብ ታዲያ፣ አሁን ላይ ግንባታው የተጀመረበትን 13ኛ ዓመት ለማክበር ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ስሰማ ስለ ታላቁ ወንዛችን ዓባይ መለስ ብዬ አንዳንድ ነጥቦችን ለማንሳት ወደድሁ ።

የዓባይ ተፋሰስ የአፍሪካን አሕጉር አንድ አስረኛ ይሸፍናል፡፡ ከዚህ ባሻገር ዓባይ በዓለማችን ከምንጩ እስከ ሜዲትራኒያን ባሕር ድረስ 6ሺህ 700 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ረዥሙ ወንዝ ነው፡፡ የዓባይ ወንዝ ሁለት ታላላቅ ገባሮች አሉት ። የዓባይ ወንዝ በዚህን ያህል ኪሎሜትሮች ሲገለጽ ከቪክቶሪያ ሐይቅ ተፋሰስ የሚነሳው ነጭ ዓባይና ከኢትዮጵያ ተራራማ ቦታዎች የሚመነጨው ጥቁር ዓባይን በማቀፍ ነው፡፡ ሆኖም ለዓባይ ወንዝ 77 ነጥብ 5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ማለትም 86 በመቶ ከእነ ለም አፈሩ በመገበር ጥቁር ዓባይ እንደ ስሙ ታላቅ ወንዝ ነው ፡፡

ለጥቁር ዓባይ የሀገር ድርሻን ስንመለከት ደግሞ 49 ነጥብ 5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ በመገበር ዓባይ ትልቁን ድርሻ ሲወስድ ፤ ባሮ አኮቦ ወንዝ 17 ቢሊዮን ሜትር ኩብ እና የተከዜ ወንዝ 11 ቢሊዮን ሜትር ኩብ በዓመት ይገብራሉ፡፡ የጥቁር ዓባይ የፍሰት መጠን ከሀገሪቱ አጠቃላይ ፍሰት ግማሽ ከመሆኑ ባሻገር፤ በጠቃሚ ማዕድናትም የበለፀገ ነው፡፡ ጥቁርና ነጭ ዓባይ ሱዳን ካርቱም ላይ ይገናኙና ዓባይ /ናይል/ ይሆናሉ ፡፡

በአንጻሩ ምንም እንኳ የዓባይ/ናይል ወንዝ የስምንት የራስጌ ተፋሰስ ሀገራት ሀብት ጭምር ቢሆንም፤ እስከ ዛሬ በብቸኝነት እየተጠቀሙ ያሉት ግን የግርጌ ተፋሰስ ሀገራት የሆኑት ሱዳንና ግብፅ ናቸው፡፡ የጋራ የውሃ ሀብት ቢሆንም የራስጌ ተፋሰስ ሀገራት እኤአ በ1929 በሱዳንና በግብፅ በቅኝ ግዛት ዘመን በተፈረመ አግላይ ስምምነት የተነሳ መጠቀም አልቻሉም። ምክንያቱም በእንግሊዝ አይዟችሁ ባይነት በተፈረመው ኢ-ፍትሐዊ ውል መሠረት ለሱዳን 4 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ፤ የተቀረውን ማለትም 48 ነጥብ 5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ለግብፅ ጀባ ብሏል፡፡

ይህ የቅኝ ግዛት ዘመን ውርዴ የሆነ ስምምነት ሱዳንና ግብፅ የራስጌ የተፋሰሱ ሀገራትን በድጋሚ በማግለል በራቸውን ዘግተው እስከ ተፈራረሙበት እኤአ 1959 ድረስ የቀጠለ ሲሆን፤ በእብሪት የተወጠረው ይህ ስምምነት፣ "ከግብፅ መንግሥት ፈቃድ ውጭ የውሃ መጠኑን

**የሚያሳዝነው እነዚህ ፍትሐዊ ያልሆኑ የፋይናንስ ተቋማት ለግብፅ ሲሆን እጃቸው ይፈታል። በዚህም ጭው ባለ በርሀ ግዙፍ መስኖዎችን፤ ሀገሪቱን ሙሉ በሙሉ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ያደረጉ ትላልቅ የውሃ ኃይል ማመንጫዎችን ገንብተዋል**

ሊቀንስ የሚችል የመስኖም ሆነ የኃይል ማመንጫ ሥራዎችን በዓባይ ገባሮችና ሐይቆች ላይ መገንባት አይቻልም፡፡" የሚልም ነው፡፡ ይህ ግብዝነትንና እብሪትን የሚያሳይ ስምምነት ታዋቂው የግሪክ የታሪክ ሊቅ ሔሮዶተስ " ግብፅ የዓባይ ስጦታ ናት፡፡" የሚለውን ይትበህል የዘነጋ ነው፡፡ እኔ ግን ግብፅ የዓባይ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ስጦታ ናት ብዬ ነው የማምነው፡፡

ይሁን ጥንታዊ ሥልጣኔዋም ሆነ የዛሬ ሕልውናዋ ከዓባይ ጋር የተቆራኘ ሆኖ ሳለ፤ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከራስጌ የተፋሰስ ሀገራት ጋር ተቀራርቦና ተባብሮ የመሥራት ፍላጎት የላትም፡፡ ይህ ፈርዖኖችም ሆኑ የዛሬዎቹ ገዥዎች ምን ያህል ከዘመኑ ጋር የመሄድና መሬት ላይ ያሉ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ለመቀበል ፍላጎቱ እንደሌላቸው ያስረዳል፡፡ ሆኖም ውሎ አድሮ ሱዳን የፍትሐዊ ተጠቃሚነት ጥያቄ ማንሳቷ አልቀረም፡፡ የ1929ኙ ስምምነት ላይ እንደገና መደራደር እንደምትፈልግ ግብፅን መወትወት ጀመረች ፡፡ የ1959ኙ የውሃ ክፍፍል ላይም ጥያቄ ማቅረብ ቀጠለች ፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ የተፋሰሱን ራስጌ ሀገራት ፍትሐዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ አዲስ ስምምነት መፈራረም ካልተቻለ ፤ ሱዳንና ግብፅ በአንድ በኩል፤ ኢትዮጵያና ሰባቱ የራስጌ ተፋሰስ ሀገራት በሌላ በኩል ለግጭት የመዳረግ እምቅ አቅም እንዳለው ቀጣናዊ የውሃ ፖለቲካ ልሒቃን ያስጠነቅቁ ይዘዋል፡፡ ከዚህ አኳያ የጋራ የሆነውን የውሃ ሀብት በጋራ መጠቀም ሲገባ፤ ግብፅ ግን ከማንኛውም ድርድር በፊት የግርጌም ሆነ የራስጌ ሀገራት የ1959ኙ ስምምነት እንዲቀበሉ ቅድመ ሁኔታ ታስቀምጣለች ፡፡

ሆኖም ይህ የግብፅ ቁሞ ቀር ቅድመ ሁኔታ በተፋሰሱ ሀገራት ተቀባይነት አላገኘም። ምክንያቱም ስምምነቶቹ የተፋሰስ ሀገራቱን በተለይ ሀገራችን ኢትዮጵያን ያላሳተፉ ከመሆኑ ባሻገር፤ ስምምነቶቹ የመንግሥታቱ ድርጅት እኤአ በ1997 ይፋ ካደረገው የፍትሐዊ የውሃ

ወደገጽ 11 ዞሯል

# የአረንጓዴ ዐሻራው ትሩፋት

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አረንጓዴ ዐሻራ ከተጀመረ ዘንድሮ 6ኛ ዓመት ላይ ደርሷል። እስካሁንም 32 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል። ለመሆኑ የአረንጓዴ ዐሻራው ፋይዳ ምንድነው?

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) 75 ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ባደረጉት ንግግር "የእኛ ዋነኛ ግብ የተራቆተውን መሬት በደን መሸፈንና የተሻለ ነገን መፍጠር ብቻ ሳይሆን ሥራችንን አረንጓዴና ከአየር ፀባይ ለውጥ ጋር በተስማማ መልኩ ማከናወን ነው፣ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ እንዳለብን የሚያሳስበን ተጨማሪ ነጋሪ አያስፈልገንም፣ ምክንያቱም የአየር ፀባይ ለውጥ የሚያስከትለውን አውዳሚ ተፅዕኖ በመላው ዓለም በተለያዩ ቦታዎች ላይ በተጨባጭ አይተነዋል" በማለት ለመርሐ ግብሩ ስኬታማነት ያላቸውን ቁርጠኝነታቸውን አስታውቀዋል።

በተባበሩት መንግሥታት የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም ዋና ዳይሬክተር ኢንገር አንደርሰን እንዳሉት፤ የአየር ንብረት ለውጥ ዓለምን ክፉኛ እየፈተነ ነው። በተለይም ለአየር ንብረት ለውጥ መዛባት እምብዛም አበርክቶ የሌላት አፍሪካ፣ በበርሃማነት መስፋፋት እና አካባቢ ብክለት ቀውሶች ክፉኛ ገፈት ቀማሽ መሆኗን ገልጸዋል።

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር የአፈር ለምነትን በመጨመር ለግብርናው ዘርፍና ለአካባቢ ሥርዓተ ምሕዳር መጠበቅ ፋይዳው የጎላ መሆኑን የጠቀሱት ኢንገር፤ ይህ ከተባበሩት መንግሥታት የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም ጋር እንደሚጣጣም እና አፍሪካውያን እያጋጠማቸው ያለውን የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ለመቀነስ ሁነኛ መፍትሔ እንደሆነ ተናግረዋል።

የአረንጓዴ ዐሻራና መሰል የአካባቢ ጥበቃ መርሐ ግብሮችን ማስፋፋት ለዓለም ኢኮኖሚ እምርታ አይተኬ ሚና እንዳላቸውም አረጋግጠዋል።

በኢትዮጵያ ደን ልማት የአረንጓዴ ዐሻራና ሰው ሠራሽ ደን መሪ ሥራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ አበሩ ጠና ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ወጣቶች ችግኝ በማፍላትና በማቅረብ፣ ጉድጓድ በማዘጋጀትና ችግኞችን በመንከባከብ የራሳቸውን ገቢ አግኝተዋል። በግላቸው ችግኝ የሚያፈሉ ወጣቶችም ዓመቱን ሙሉ የዛፍ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ችግኞችን ለግለሰቦችና ድርጅቶች በመሸጥ ገቢያቸውን ከፍ አድርገዋል።

ከዚህ ባለፈ ተጠቃሚዎች ችግኞቹን በአደባባዮች፣ በፓርኮችና፣ በመኖሪያ ቤታቸውና በሥራ ቦታቸው ላይ በመትከል የአካባቢውን ውበት መጠበቅና በምግብ ራስን መቻል ይገባል ያሉት አቶ አበሩ፤ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብሩ ስኬት አስተማማኝ እንዲሆን የተተከሉትን ችግኞች በባለቤትነት ማስተዳደርና መንከባከብ ያለበት የየአካባቢው ነዋሪ መሆን እንዳለበት ተናግረዋል።

በዘንድሮው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በሀገር አቀፍ ደረጃ 6 ነጥብ 5 ቢሊየን ችግኝ ለመትከል ዝግጅት እየተደረገ እንደሆነም አቶ አበሩ ጠቁመዋል።

# "የመደመር ትውልድ"...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ተቋሙ እያካሄደ ያለውን ሪፎርም መሠረት በማድረግ ለሀገር የሚጠቅሙ ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ ሀገራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን አመላክተዋል።

በዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ እምርታ አስፋው፣ ትረካው በዘመኑ የሚስተዋለውን የንባብ ዝንባሌ፣ የጊዜ ሁኔታ፣ የማኅበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተዘጋጀ ነው ብለዋል።

ዘመኑን የዋጀ ሥራ ማምጣት አስገዳጅ እየሆነ መምጣቱን የገለጹት ምክትል ሥራ አስፈጻሚዋ፤ የመደመር ትውልድ በድምፅ መምጣቱ የማንበብ ጊዜ ለሌላቸውና በተለያዩ ምክንያቶች ማንበብ ለማይችሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ እንደሚያደርግ ጠቅሰዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ለማንበብ የጊዜ እጥረት




ለሚያጋጥማቸው በድምጽ የሚተላለፈውን ትረካ በመስማት ከመጽሐፉ ግንዛቤ ለመውሰድ ያስችላል ብለዋል፡፡

የድምፅ ትረካው በሚዲያው ባለሙያዎች አማካኝነት ያለምንም ወጪ ሥራው ተጠናቆ ለአድማጭ ተመልካች መድረሱን የገለጹት ወይዘሮ እምርታ፤ ትረካውም በአዲስ ዋልታ 105.3 ኤፍ ኤም በቋሚነት እንደሚተላለፍ፤ በቀጣይም በኦውዲዮ ቡክ እንዲሁም አኒሜሽኖችና ከትረካው የተቀነጨቡ ሀሳቦችን በዩቱብ ገጽ እንዲሁም በቴሌቪዥንና የተለያዩ የማኅበራዊ ሚዲያ አማራጮች ተደራሽ እንደሚሆን አስታውቀዋል፡፡

በአዲስ ዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት የተሰናዳው ሁነት ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ ወጣቶችና ታዋቂ ግለሰቦች በተገኙበት በዓድዋ ድል መታሰቢያ ተካሂዷል፡፡ በምረቃው ሥነሥርዓት ላይ መጽሐፉ ከያዛቸው አንኳር ጉዳዮች ላይ በተቀነጨቡ ሃሳቦች ዙሪያ ላይ የፓናል ውይይት ተካሂዷል፡፡

የመደመር ትውልድ 274 ገፆች ያሉት፤ በሦስት ክፍሎችና በ10 ምዕራፎች የተዋቀረና በተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው፡፡

# የሀገር መከላከያ ሠራዊት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ማድረግ አለባችሁ ሲሉ አሳስበዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሠላም ማስከበር ማዕከል አዛዥ ሜጀር ጄኔራል አዳምነህ መንግሥቴ በበኩላቸው፤ ለሠራዊታችን ከተሰጡት ተልዕኮዎች አንዱ በአካባቢ፣ በአሕጉራዊና በዓለም አቀፋዊ የሠላም ማስከበር ግዳጆች በብቃት መሳተፍ ነው፡፡ በዚህም መልካም እሴቶችን በመላበስ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የትኛውንም ግዳጅ በጀግንነት የመወጣት ብቃቱ በዓለም ማኅበረሰብ ዘንድ ተመራጭ የሠላም አስከባሪ እንዲሆን አስችሎታል ብለዋል፡፡

"በአህጉራችን እየተባባሰ የመጣውን የእርስ በእርስ ግጭት ለማብረድ የሚደረገው ትግል በአካባቢው ያለው የኃያላን ሀገራት ሽኩቻ ተጨምሮበት ግዳጃችሁን ውስብስብ ያደርገዋል" ያሉት ሜጀር ጄኔራሉ፤ ሁኔታውን ተገንዝባችሁ በተሠማራችሁበት የግዳጅ ቀጣና ተልዕኳችሁን በጥንቃቄ መከወን ይገባችኋል ሲሉ ተመራቂዎቹን አሳስበዋል፡፡

ሠራዊቱ በተለያየ ግዳጅ ላይ የቆየና የተለያየ አቋም የነበረው በመሆኑ በተሰጠው ሥልጠና አንድ አይነት አስተሳሰብ፣ የአካል ብቃትና አቋም እንዲኖረው መደረጉን እና ለየትኛውም አይነት ተልዕኮ ዝግጁ መሆኑን የገለጹት ደግሞ ወደ ጁባ ከሚያቀኑት ሁለት ሻለቆች አንዱ የሆነው የ18ኛ ሞተራይዝድ ሻለቃ አስተዳደር ሌተናል ኮሎኔል ካሡ ሺበሺ ናቸው፡፡

ከሀገራችን ወደ ደቡብ ሱዳን ጁባ የምንጓዘው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሠላም አምባሳደር ሠራዊት ሆነን ነው ያሉት ኮሎኔሉ፤ "የተሰጠንን ተልዕኮ በድል ተወጥተን በመመለስ የሀገራችንን ሥም እንደምናስጠራ እርግጠኛ ነኝ" ብለዋል፡፡

በዕለቱ ከተመረቁት የሠላም አስከባሪ አባላት አንዱ የሆኑት ሻለቃ ፋሲል ይግዛው፤ በደቡብ ሱዳን ጁባ ስንሠማራ በተማርነው ትምህርትና በወሰድነው ሥልጠና መሠረት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ማዕቀፎች ግዳጆችንን በብቃት በመወጣት የአካባቢውን ሠላም ለማረጋገጥ ተዘጋጅተናል ብለዋል፡፡

ተመራቂዎቹ ለአራት ወራት ግዳጃቸውን በብቃት መወጣት የሚያስችላቸው በንድፈ ሀሳብ፣ በተግባር ልምምድ እና በተለያዩ የግዳጅ ተሞክሮች የተደገፈ ሥልጠና በመውሰድ ከፍተኛ አቅም መገንባታቸውን በተግባር ማሳየታቸው በምረቃ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ተገልጿል።

ትናንት የተመረቁት የሠላም አስከባሪ አባላት 1ሺህ 493 ሲሆኑ፣ ኢትዮጵያ እስካሁን በተለያዩ ዙሮች 9ሺህ 293 የሠላም አስከባሪዎችን ወደ ደቡብ ሱዳን መላኳም በምረቃ መርሐግብሩ ላይ ተነግሯል።

# ሀገር በቀል..

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የገንዘብ ሚኒስትር አቶ አሕመድ ሽዴ ገለጹ። የከፍተኛ አመራሮችና አጋር አካላት የልማት ፎርም ትናንት ተካሂዷል።

አቶ አሕመድ ሽዴ መድረኩን በንግግር ሲከፍቱ እንደገለጹት፤ ለውጡን ተከትሎ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ወደ ትግበራ ገብቷል። ሪፎርሙ በተጀመረ ማግስት ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ትግበራው ላይ ጫና ቢፈጥሩም የልማት አጀንዳውን ወደፊት ለማራመድ በተደረገው ሰፊ ጥረት አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል።

ኢትዮጵያ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ለመፍጠር፣ የተቀላጠፈ የንግድ አሠራር ሥርዓት ለመዘርጋትና ተቋማዊና በግሉ ዘርፍ የሚመራ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ የሚያስችል ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ቀርጻ ወደ ሥራ መግባቷን አስታውሰዋል።

ይሁን እንጂ ሪፎርሙ ይፋ በተደረገ ማግሥት የተከሰቱት ኪቪድ 19 እና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተያያዙ ችግሮች ለሪፎርሙ ተግዳሮቶች እንደነበሩ አንስተዋል።

በተጨማሪም በምሥራቅ አውሮፓ የተከሰተው ጦርነት፣ ያደጉ ሀገራት በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ላይ የሚከተሉት ጥብቅ የገንዘብ ፖሊሲና ተያያዥ ጉዳዮችም ሪፎርሙ ላይ የራሳቸውን ጫና አሳድረዋል ብለዋል።

በውስጣዊና ውጫዊ ጫናዎች ውስጥም ቢሆን በመንግሥት ያላሰለሰ ጥረትና በአጋር አካላት ድጋፍ አመርቂ ውጤት መመዝገቡን ጠቅሰው፤ በዚህም የነፍስ ወከፍ ገቢ በማሳደግ የተሻሻለ የብድር አስተዳደር በመፍጠር፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና ወጪ ምርት በመጨመርና ሌሎች ስኬቶችን በማስመዝገብ ውጤት መገኘቱን አስታውቀዋል።

ኢኮኖሚው ላይ ስኬቶች መኖራቸውን ያህል አሁንም ብዙ ሥራ የሚጠይቁ ጉዳዮች መኖራቸውን አስታውሰው፤ ለዚህም ሁለተኛውን የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ሪፎርም ወደ ትግበራ መግባቱን ገልጸዋል።

ሠላምን ለማረጋገጥና በግጭት የተጎዱ ማኅበረሰቦችን መልሶ ለማቋቋም በትኩረት እየተሠራ መሆኑንም አመላክተው፤ በአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ተቀርጾ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል። በዚህም በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር የተራቆቱ መሬቶችን እንዲያገግሙ የማድረግ፣ ታዳሽ ኃይል የማመንጨት አቅምን የማሳደግና ሌሎችንም ሥራዎች እየሠራች ትገኛለች ብለዋል።

ይሁን እንጂ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ለመቋቋም አሁንም ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል ሲሉ አመላክተዋል።

የሀገሪቱ ቀዳሚ የልማት አጀንዳዎች ላይ የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ ጠንካራ ሥራ፣ ትብብርና መቀናጀትን እንደሚጠይቅ የጠቆሙት አቶ አሕመድ፤ መንግሥት ያለውን ዓለም አቀፍ ግንኙነትና ቀጣናዊ ትብብር በአዲስ መንፈስ ለማጠናከር እየሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

በትናንትናው ዕለት የተካሄደው የከፍተኛ አመራሮችና የአጋር አካላት የልማት ፎርም ዘላቂ ሰላም ማስፈን፣ ጠንካራ ማክሮ ኢኮኖሚ መገንባትና የመቋቋም አቅምን ማሳደግ ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን፤ በጉዳዮች ዙሪያ ማብራሪያ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል።

ፎረሙ በኢትዮጵያ መንግሥትና በልማት አጋሮች መካከል በሀገሪቱ ቀዳሚ የልማት ትኩረቶችና ራዕይ ላይ የጋራ መግባባት ለመፍጠር ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ተገልጿል። በመድረኩ ሚኒስትሮች፣ የክልል ፕሬዚዳንቶች፣ የልማት አጋሮችና ሌሎችም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተሳትፈዋል።

# "ማዕከሉ እንደሀገር ያለውን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ያለውን ስብራት ለመጠገን ይረዳል ሲሉ ተናግረዋል።

በማዕከሉ አማካኝነት በዓመት 10 ሺህ ሴቶችን ካሉበት የኑሮ ሁኔታ አውጥቶ የተሻለ ሥራ ማስያዝ የምንችል ከሆነ 10 ማዕከል ከገነባን ደግሞ በዓመት 100 ሺህ ሴቶችን ወደተሻለ ሕይወት መመለስ እንችላለን ብለዋል፡፡

የማዕከሉ መገንባት በተለያዩ ምክንያቶች ለማኅበራዊ ችግሮች የተጋለጡ ሴቶችን ተሐድሶ በመስጠት መልሶ ለማቋቋም የሚረዳ መሆኑን ገልጸው፤ በዚህም በዓመት 10 ሺህ የሚደርሱ ሴቶችን ከጎዳና ሕይወት አውጥቶ የተሻለ ሥራ ማስያዝ የሚያስችል በመሆኑ ስብራታችንን ለመጠገን እድል ይፈጥራል ሲሉ አስረድተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደተናገሩት፤ አሻግሮ የመመልከትና ትውልድን ማዕከል አድርጎ ያለመሥራት እንደሀገር ካሉብን ስብራቶች መካከል የሚጠቀስ ነው። ትልቁም ትንሹም፣ ሀብታሙም ድሃውም፣ ወጣቱ፣ የተማረውም ሆነ ያልተማረው ዛሬ ላይ ስለሚያገኛት ነገር እንጂ ነገን እያሰበ አለመሥራቱ ጉዳት ነው ሲሉ ጠቁመዋል።

ማዕከሉ የኢትዮጵን ስብራት ለመጠገን ከሚያበረክተው አስተዋፅዖ ባለፈም ነገ ከነገወዲያም መሰል ፕሮጀክቶችን በኅብረት ለመሥራት ስንቅ የሚሆን ነው ብለዋል፡፡

ሴቶች በኢትዮጵያ ግማሽ ቁጥር ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ በሁሉም ሥራዎች ያላቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑን አስታውሰው፤ እነሱንም ማሰብ፣ ማነጽ፣ ማስተማርና ዕድል መስጠት ካልቻልን እንደሀገር ለመለወጥ ያለን ሕልም ሙሉ አይሆንም ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ባልተገባ መንገድ ሕይወታቸውን የሚመሩ ሴቶችን ወደተሻለ ሕይወት ስንመልስ እነርሱን ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር ያለብንን የስክነት፣ የማሰብ፣ የማስተዋል፣ አርቆ የመመልከት ስብራት ለመጠገን ማዕከሉ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያበረክት አብራርተዋል፡፡

በአዲስ አበባ የታሪክ ስብራታችንን ለመጠገን የዓድዋ ሙዚየምን ጨምሮ፣ ወዳጅነት፣ እንጦጦና አንድነት ፓርክን፣ አብርሆት ቤተ መጽሐፍትን፣ መስቀል አደባባይ እና ሌሎች በርካታ ፕሮጀክቶች መገንባት እንደተቻለ አንስተዋል።

በአዲስ አበባ የተገነቡት ሁሉም ፕሮጀክቶች ቢደመሩ "ለነገዋ" የሴቶች ተሐድሶና ክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከልን ያክል ግዝፈት እንደሌላቸው አመላክተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አበቤ በበኩላቸው፤ ማዕከሉ በተለያዩ ምክንያቶች ለማኅበራዊ ችግሮችና ለወሲብ ንግድ ለተጋለጡ ሴቶች ተሐድሶ በመስጠት መልሶ ለማቋቋም የሚረዳ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ማዕከሉ በየዓመቱ ለ10 ሺህ ሴቶች ሥልጠና በመስጠት በዘላቂነት እንዲቋቋሙና ገቢ እያገኙ ራሳቸውን እንዲችሉ እገዛ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል፡፡

ወጣት ሴቶቹ በማዕከሉ ቆይታቸው ከሚያገኙት የሥነ-ልቦና ድጋፍ በተጨማሪ የሥነ-ውበት፣ የከተማ ግብርና፣ የምግብ ዝግጅት፣ የፀጉር ሥራ፣ የእንጨት ሥራዎች፣ የልብስ ስፌት፣ የከተማ ውበት አጠባበቅና የኮምፒዩተር ሙያ ሥልጠና ወስደው ወደ ሥራ እንዲገቡ ይደረጋል ብለዋል፡፡

ማዕከሉ በውስጡ የተሐድሶ ሥልጠና የሚሰጥባቸው የክህሎት ማበልፀጊያ፣ የማሠልጠኛ ማዕከላት፣ የሥነ-ልቦናና የምክር አገልግሎት፣ የሕክምና ማዕከል፣ ማደሪያ ክፍሎች፣ መመገቢያ አዳራሾች እንዲሁም የስፖርት ማዘውተሪያና የመዝናኛ ስፍራዎችን ማካተቱን ገልጸዋል፡፡

# በሀገር ፍቅር ስሜት የበጎ አድራጎት ስራን የጀመረው ድርጅት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ዓለማችን ‹‹ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው›› ለሚለው አባባል ተገዢ የሆኑና ሰው መሆናቸውን በተግባር የሚያሳዩ በርካታ ሰዎች አሏት፡፡ እነዚህ ሰዎች ሰው በመሆናቸው ብቻ ሰው ለተባለ ፍጡር ሁሉ በጎ ያደርጋሉ፡፡ እንዲህ አይነት ሰዎች የእኔ የሚሉት አይኖራቸውም፡፡ ሁሉም የእነሱ እነሱም የሁሉም ናቸው፡፡ እንዲህ አይነቱ ተግባር የእምነት አገር ናት በምትባለው ኢትዮጵያ እዚህም እዚያም ይስተዋላል። ኢትዮጵያውያን በጋራ አብሮ የመኖር የቆየ ባህል ያላቸው በመሆኑ መረዳዳት፣ መተጋገዝና መደጋገፍ ጠንካራ ባህላቸው ነው፡፡

በአገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች መቋቋማቸውም የኢትዮጵያውያኑ አብሮ የመኖር የቆየ ባህላቸው የወለደው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ‹‹የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ›› እንዲሉ በርካታ ኢትዮጵያውያን የበጎ አድራጎት ድርጅት በማቋቋም ወንድም እህቶቻቸውን፤ እናትና አባቶቻቸውን እንዲሁም ለችግር የተጋለጡ ሕጻናትን ጭምር ከወደቁበት አንስተው የነገ ተስፋቸውን ብሩህ ሲያደርጉ ማየት የተለመደ ነው፡፡

የዕለቱ እንግዳችን ‹‹ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው›› በማለት በሀገር ፍቅር ስሜት ተነሳስቶ ወደ በጎ ሥራ በተሰማራ ቤተሰብ ነው፡፡ ቤተሰቡ ለዓመታት ይኖር ከነበረበት ሀገረ አሜሪካ ወደ ሀገሩ ጠቅልሎ በመግባት በርካታ የበጎ አድራጎት ሥራዎችን እየሠራ ይገኛሉ፡፡

ቤተሰቡ ከተሰማራባቸው የበጎ አድራጎት ሥራዎች መካከልም በኤች አይ ቪ ኤድስ ምክንያት ለተለያዩ ችግሮች የተዳረጉ ዜጎችን በመደገፍ የሚሠሩት ሥራ አንዱ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ የሚሰራው ቤዛ የተሰኘው የበጎ አድራጎት ድርጅት ከተመሰረተ 17 ዓመታትን አስቆጥሯል፤ በኤች አይ ቪ ኤድስ ሳቢያ ለተለያዩ ችግሮች በተጋለጡ ሴቶችና ሕጻናት ላይ ትኩረት አድርጎ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ድርጅቱ በተለይም በኤች አይ ቪ ኤድስ ሳቢያ ተስፋ ከቆረጡ ሴቶች ጎን በመሆን ‹‹አይዟችሁ፤ ሁሉም ያልፋል፤ መኖር ይቻላል፤ በርቱ ተበራቱ›› ያለ ድርጅት ስለመሆኑ የቤዛ ኢንተርናሽናል ኮሚኒቲ ዴቨሎፕመንት መስራችና ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም ባለራዕይ ወይዘሮ ሶፊያ አሰፋ ይናገራሉ፡፡

ወይዘሮ ሶፊያ እንዳሉት፤ ድርጅቱ የተቋቋመው በቤተሰብ ነው፤ ሥራውን የጀመረውም በ1999 ዓ.ም ሲሆን፣ ሕጋዊ ፈቃዱን በ2000 ዓ.ም ነው የወሰደው፡፡

እሳቸው ባለቤታቸውንና ልጆቻቸውን አጋር አድርገው የበጎ አድራጎት ድርጅቱን በቤተሰብ ሲያቋቁሙ መነሻ ሃሳባቸው ከውስጥ የመነጨ የአገር ፍቅር ስሜት ነው፡፡ በትምህርት ምክንያት ከሀገር ወጥተው አራት አስርት ዓመታትን ያሳለፉት ወይዘሮ ሶፊያ፤ በእነዚህ ሁሉ ዓመታት አንድም ቀን አገራቸውን ዘንግተው አያውቁም፡፡

ቤተሰቡ አንዱን ቀዳዳ ደፈንን ሲል ሌላኛው ቀዳዳ እያፈሰሰ 42 ዓመታትን በባዕዳን ሀገር ሊያሳልፍ ተገዷል፡፡ እሳቸውም ያኔ ስለ አገራቸው የሚሰሙት ሁሉ ያሳምማቸው ነበር፡፡ ከ42 ዓመታት ቆይታ በኋላ ግን ወደ እናት አገራቸው ጠቅልለው ለመምጣት ወቅታዊ ሁኔታው ያስገደዳቸው በመሆኑ ወደ አገራቸው ተመለሱ። በወቅቱ በባዕድ አገር ሆነው ሲያደምጡት የነበረውና በአገሪቱ ውስጥ ያለው ችግር ከወሬ አልፎ ስጋ ለብሶ አይኑን አፍጥጦና ጥርሱን አግጦ ተመለከቱት፡፡ ይህን ጊዜ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለባቸው ወስነው ሰዎችን ለመርዳት ከውስጥ በመነጨ ፍላጎትና በአገር ፍቅር ስሜት አንድ ብለው ጉዞ ጀመሩ፡፡

ወቅቱ አንድ ትውልድን እምሽክ አድርጎ እንደጨረሰ የሚነገርለት የኤች አይ ቪ ኤድስ

**የእነዚህ ህብረተሰብ ክፍሎች ውጤታማነት ሌሎች ተስፋ ያነገቡ ዜጎችን እየወለደና ባለራዕዮችን እየፈጠረ እስካሁን 11 ሺ የሚደርሱ ሴቶች ከድርጅቱ ባገኙት ስልጠናና የገንዘብ ድጋፍ ራሳቸውን የቻሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል**

በሽታ የተስፋፋበትና ብዙዎችን የጨረሰበት ወቅት እንደነበር ወይዘሮ ሶፊያ ያስታውሳሉ፡፡ በሽታው በተለይም ወጣቱን ትውልድ በብርቱ የጎዳ በመሆኑ አብዛኛው ወጣት በፍርሃት የተሸበበበትና ቆፈን ውስጥ የነበረበት ጊዜ ነበር። በወቅቱም የመጀመሪያ ሥራቸው ማስተማርና ግንዛቤ መፍጠር መሆን አለበት ብለው በማመን በተለይም ወጣቱን ሰብስቦ ማስተማርና ግንዛቤ መፍጠር ላይ ትኩረት አድርገው መስራት ጀመሩ።

‹‹ወጣቱ ከተማረና ግንዛቤ ከተፈጠረለት የገባበትን ችግር መረዳት ይችላል፡፡ ከዚህ አለፍ ሲልም የሚፈጠርለትን አጋጣሚ በመጠቀም ራሱን ማዳን ይችላል›› በሚል ዕምነት ወደ ሥራው የገቡት ወይዘሮ ሶፊያ፤ ወጣቶችን አሰባስበው የሚሰጡት ትምህርትም መሰረቱን በታላቁ ቅዱስ መጽሐፍ ላይ በማድረግ ለሕይወት አስፈላጊና ገንቢ የሆኑ ትምህርቶችን ይሰጡ እንደነበር ነው ያጫወቱን፡፡ ወጣቱን በስነ ምግባር በማነጽ የሕይወት መርሆዎችን በማስታጠቅ፤ በተለይም ታማኝ ዜጋ እንዲሆንና ለሀገሩ መጻለይ እንዲችል በማስተማር በርካታ ወጣቶችን ከገቡበት ድባቴ ማውጣት እንደቻሉ ይናገራሉ፡፡ መነሻቸውን ወጣቶች ላይ ያደረጉት ወጣቶች ለብዙ ችግር ተጋላጭ ከመሆናቸው ባለፈ የነገ ሀገር ተረካቢ እነሱ በመሆናቸው መሆኑን ጠቅሰው፣ በእነሱ ላይ መስራት የግድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ወደ ሀገራቸው የተመለሱበት ወቅት ኤች አይ ቪ ኤድስ የተስፋፋበትና አብዛኛውን ወጣት ተስፋ ቢስ ያደረገበት ወቅት እንደነበር ያስታወሱት ወይዘሮ ሶፊያ፤ በወቅቱ ለኤች አይ ቪ ኤድስ የተዳረገው አብዛኛው ወጣት የሚገኘው እንጦጦ ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን እንደነበር ተናግረዋል፡፡ በጊዜው እርሳቸው ቤተሰባቸውን ይዘው ወደ ስፍራው ባቀኑበት አጋጣሚ በርካታ ወጣቶች በፕላስቲክ ቤት ሰርተው ይመለከታሉ። በስፍራው የነበሩት አብዛኞቹ ወጣቶች ወደ ሥፍራው ያቀኑት በእምነታቸው ተስፋ በማድረግ ለመዳን ጓጉተው እና ከቤተሰብ ሸሽተው ነው፡፡ ‹‹በወቅቱ ከወጣቶቹ መረዳት የቻልኩት የመዳኛ አልያም የመሞቻ ቀናቸውን በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን ነው›› የሚሉት ወይዘሮ ሶፊያ፣ በርካታ ችግሮችን እንዳሳለፉ ተናግረዋል፡፡

በኤች አይ ቪ ኤድስ የተያዘ ሊታከምበት የሚችል መድሃኒት ምንም አይነት መዳህኒት አለመኖሩም ችግሩን ይበልጥ እንዳወሳሰበው ይናገራሉ፡፡ መገለልና መድሎው ከበሽታው በላይ ወጣቱን እንደጎዳውም ነው የገለጹት። እሳቸው እንዳሉት፤ በጸበል መዳንን ተስፋ አድርገው በእንጦጦ ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን ደጃፍ የተጠለሉና በፕላስቲክ ቤት ሰርተው የሚኖሩ ከአራት ሺ በላይ ዜጎችን ቦታው ድረስ ሄደው ተመለከቱ፡፡ ከዛም አንድ ነገር ማድረግ እንዳለባቸው በማመን በመጀመሪያ ወደ እነሱ በመቅረብ የመገለል ስሜት እንዳይሰማቸው በማድረግ ማስተማርና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ሰጡ፡፡

በዋናነት መኖር እንደሚቻልና ተስፋ እንዳይቆርጡ ለማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት የጀመሩት በእንጦጦ ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ በተፈቀደላቸው አዳራሽ እንደነበር ያስታወሱት ወይዘሮ ሶፊያ፤ በቦታው ያሉትን ሰዎች በሙሉ ሰብስቦ በማስተማርና የምግብ አቅርቦት ተደራሽ በማድረግ ሥራው መጀመሩን ነው ያስረዱት። እንዲህ እያለ የተጀመረው የበጎ አድራጎት ሥራ ድርጅት በማቋቋም ከማስተማር ባለፈ የተለያዩ ስልጠናዎችን ማለትም የጌጣጌጥ፣ የስፌት፣ የቆዳ፣ የሸክላና ሌሎችም የእጅ ሥራዎችን በማሰልጠን ወጣቶቹ ሥራ መፍጠር እንዲችሉ እገዛ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በወቅቱ ስልጠና ወስደው ወደ ሥራ የገቡት 50 ሴቶች እንደነበሩ ያስታወሱት ወይዘሮ ሶፊያ፤ ሴቶቹ ድርጅቱ ያመቻቸላቸውን የተለያየ የሙያ ስልጠና እንዲሁም መጠነኛ የሆነ መነሻ ካፒታል ይዘው ወደ ሥራ እንዲገቡና የገቢ ምንጭ እንዲያገኙ በማድረግ ራሳቸውን እንዲችሉ አድርጓል፡፡ ራሳቸውን ከመቻል ባለፈም ነገን ተስፋ ማድረግና መኖር እንደሚቻል ማሳያ ሆነው የነገ ተስፋቸውን ብሩህ ለማድረግ በሚያደርጉት ጥረት ውጤታማ መሆን ችለዋል፡፡ ውጤታቸው ሌሎች ተስፈኞችን እየወለደና ባለራዕዮችን እየፈጠረ እስካሁን 11 ሺ የሚደርሱ ሴቶች ከድርጅቱ ባገኙት ስልጠናና የገንዘብ ድጋፍ ራሳቸውን ችለው ወጥተዋል፡፡

በአሁን ወቅትም በቤዛ ኢንተርናሽናል የበጎ አድራጎት ድርጅት ውስጥ ሕጻናትን ጨምሮ 200 የሚደርሱ ተገልጋዮች አሉ፡፡ የሚሉት ወይዘሮ ሶፊያ፤ ድርጅቱ በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኝ ሲሆን፣ ከክፍለ ከተማው ጋር ይሰራል፡፡ ክፍለ ከተማው በአካባቢው የሚገኙ እገዛና ድጋፍ የሚሹ ሴቶችን መልምሎ የሚሰጣቸው ሲሆን፤ በተለይም በኤች አይ ቪ ኤድስ የተያዙ እናቶችና ሕጻናት ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ሲሆን በአብዛኛው ሴቶች ተጋላጭ እንደሆኑም ተናግረዋል፡፡ እነዚህ ሴቶችም የተለያዩ ስልጠናዎችን እየወሰዱ ይገኛሉ።

ከዚህ ቀደም የድርጅቱን አገልግሎት አግኝተው እራሳቸውን ችለው የወጡት ዜጎች ጭምር በድርጅቱ እያገለገሉ መሆኑን የገለጹት ወይዘሮ ሶፊያ፤ በማስተማር፣ ስልጠና በመስጠትና በተለያየ አገልግሎቶች እገዛ እያደረጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ድርጅቱ በተለይም የጌጣጌጥና የእጅ ሥራ ስልጠናዎችን የሚሰጥ እንደመሆኑ የሚመረቱ ጌጣጌጦችና የተለያዩ የእጅ ሥራዎቹ በመሸጥ ገቢ የሚያገኝ እንደሆነም ተናግረዋል። ከዚህ ቀደም ምርቶቹን ለውጭ ገበያ ያቀርቡ እንደነበር ያስታወሱት ወይዘሮ ሶፊያ፤ በአሁን ወቅት ግን መንግሥት ባወጣው ሕግ መሰረት ለውጭ ገበያ አይቀርብም ነው ያሉት፡፡

በድርጅቱ ከሚመረቱት ጌጣጌጦች መካከል ከጥይት ቀለሃ የሚሰሩ የተለያዩ ጌጣጌጦች ማለትም የአንገት፣ የእጅ፣ የጆሮ፣ የእግርና ጌጣጌጦች ይገኙበታል፡፡ ከጌጣጌጥ በተጨማሪም የሸክላ ሥራዎችንና የስፌት ሥራዎችን በተለያየ ዲዛይን እየሰሩ ለገበያ ያቀርባሉ፡፡ የገበያ መዳረሻዎቻቸውም ባዛርና ኤግዚቢሽኖች ጨምሮ በመሸጪያ ሱቆች እንደሆነ ነው የገለጹት፡፡

ከድርጅቱ ባገኙት የስልጠናና የማማከር አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነው የተለያዩ ምርቶችን እያመረቱ በመሸጥ የገቢ ምንጬ አግኝተው ራሳቸውን የቻሉና ነገን በብዙ ተስፋ የሚጠባበቁ በርካታ ውጤታማ ሴቶች ስለመኖራቸው የገለጹት ወይዘሮ ሶፊያ፤ ለእዚህም ሽሮሜዳ አካባቢ ሱቅ ከፍተው ቡና በማፍላት፣ የሸክላ ሥራዎችን አምርተው በመሸጥና በሌሎች ሥራዎች የተሰማሩ ሴቶች ማሳያ ናቸው ብለዋል፡፡

ድርጅቱ የበጎ አድራጎት ሥራውን ሲጀምር ወቅቱ ኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ የተስፋፋበትና ሰዎች የሚገለሉበት በመሆኑ በርካታ ችግሮችን እንዳሳለፉ ጠቅሰው፣ የእዚህ ችግር ሰለባዎች አብዛኞቹ ወጣቶች እንደነበሩና ታሪካቸው እጅጉን ልብ የሚነካ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ አንዳንዶቹ ከዩኒቨርሲቲ የወጡና ቤተክርስቲያን ውስጥ የተሸሸጉ ነበሩ፡፡ የሚላስ የሚቀመስ ሲያጡም ተሸፋፍነው ልመና ይወጡ እንደነበሩም አጫውተውናል፡፡ በወቅቱ ለበሽታው የተሰጠው ስዕል እጅግ በጣም አስፈሪና አስከፊ በመሆኑ ብዙዎች ከድርጅቱ አቅም በላይ በሆነ ምክንያት በሕይወት ተለይተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከተለያዩ አጋዥ ድርጅቶች በሚገኝ የገቢ ድጋፍ አንዳንድ መድሃኒቶችን በማቅረብም ጥቂት የማይባሉ ሰዎችን መታደግ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

ይሁንና አሁን ላይ ማኅበረሰቡ ስለበሽታው ያለው ግንዛቤ ከፍ ያለ በመሆኑ መድሃኒቱ በስፋት ተለምዷል የሚሉት ወይዘሮ ሶፊያ፤ አሁን ጊዜው ተሻሽሏል የሰዎች ግንዛቤ አድጎ የተሻለ ጊዜ ላይ ደርሰናል በማለት ገልጸዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ አሁን ደግሞ መዘናጋት ተፈጥሯል፤ መዘናጋቱ ችግሩ ካለፈው ጊዜ ባልተናነሰ ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ እንደሆን እያረገው ነው ይላሉ፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ብዙዎች እየተዘናጉ ነው፡፡ ስለዚህ ወጣቱን ማነቃቃትና ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ ኤች አይ ቪ ኤድስ ዛሬም ብዙዎችን እየጨረሰ ነው፡፡ ሰዎች እጅግ ተዘናግተዋል። መድሃኒቱ ፈዋሽ አይደለም፡፡ ስለዚህ ይህን በመረዳት ማኅበረሰቡ ጥንቃቄ እንዲያደርግ የሚመለከታቸው አካላት በተለይም ጤና ሚኒስቴርና ትምህርት ሚኒስቴር ሰፊ ሥራ መሥራት እንዳለባቸው አመላክተዋል፡፡

በቀጣይ በተለይም ወጣቱ ላይ ሰፊ ሥራ የመሥራት ዕቅድ ያላቸው ወይዘሮ ሶፊያ፤ ድርጅቱ መገናኛ አካባቢ የማገገሚያ ማዕከል እያስገነባ መሆኑን ጠቁመዋል፤ ግንባታው ሲጠናቀቅ በወጣቱ ባህሪና ስነምግባር ቀረጻ ላይ ትኩረት ያደረጉ ስልጠናዎችን በተለያየ መንገድ እንደሚሰጥ ተናግረዋል፡፡ የበጎ አድራጎት ሥራ በበጎ ፈቃድ ላይ ተመስርቶ የሚሰራ ሥራና ከፍተኛ የሆነ ወጪ የሚጠይቅ እንደመሆኑ መንግሥትን ጨምሮ እያንዳንዱ ግለሰብ የበኩሉን መወጣት ከቻለ ብዙዎች ዘንድ መድረስ እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

‹‹መኖር ማለት ለኅብረተሰብ መፍትሔ መሆን ማለት ነው›› የሚሉት ወይዘሮ ሶፊያ፤ ድርጅቱ በሚሰራቸው የበጎ ሥራዎች በተለይም ብዙዎች ከገቡበት ድባቴ ወጥተው ዛሬን መኖር መቻላቸውና ነገን በተስፋ መጠባበቃቸው ከፍተኛ የሆነ የመንፈስ እርካታን እንደሚሰጣቸው ገልጸዋል፤ ይህም አንዱ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ እንደሆነና በጎ ማድረግ ለራስ እርካታና ለእግዚአብሔር ብድራት መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## በሰው ሰራሽ አስተውሎት የአፈርን ይዘት የማወቂያ ቴክኖሎጂን የፈጠረ ወጣት

**ክብረአብ በላቸው**

አዲስ የፈጠራ ሥራ ወይም ቴክኖሎጂ የሰው ልጆችን ሕይወት በብዙ መልኩ ቀይሯል። ከትምህርት፣ ከጤና፣ ከግብርና እና ከሌሎች ዘርፎች አንፃርም የሚሰጠውን ጠቀሜታ ሲታይ እጅግ አስገራሚ ደረጃ ላይ እየደረሰ ይገኛል፡፡ የአጠቃቀም ሂደቱን ሲቃኝ እንደ ዘርፎቹ አይነት ጥቅም ላይ የሚውልበት መንገድም ይለያያል፣ ጥቅም ላይ የሚውሉት መሳሪያዎችም እንዲሁ እንደ አገልግሎቱ አይነትና ስፋት ይለያያሉ፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ላሉና በማደግ ላይ ለሚገኙ ሀገራት ደግሞ የቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራ ፋይዳው እጅግ የጎላ ነው።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች ላይ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የማደግ ዕድል ያላት ሲሆን፣ የማኅበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ ለመሻሻል፣ ለደህንነት፣ ለትምህርት ተደራሽነት፣ ለግብርና እና ለጤና አገልግሎት እንዲሁም በአጠቃላይ በሁሉም ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን በቴክኖሎጂና በአዲስ የፈጠራ ሥራ መታገዝ የግድ ሆኗል፡፡ በተለይ አሁን አሁን ያለ ቴክኖሎጂ መኖር ከባድ እየሆነ መጥቷል። ከእነዚህ ዘመን አፍራሽ የቴክኖሎጂ ዘርፎች መካከል አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ወይም የሰው ሰራሽ አስተውሎት ቀደሚውን ስፍራ እየያዘ መጥቷል።

ሰው ሰራሽ አስተውሎት በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ዘርፎች ምርታማነትን ለመጨመር እንዲሁም አምራች እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ለማስተሳሰር ቁልፍ ቴክኖሎጂ ነው። ሰው ሰራሽ አስተውሎት በአሁኑ ወቅት በትምህርት፣ በኢንዱስትሪ፣ በጤና፣ በደህንነት እና በግብርና ዘርፎች ምርታማነትን እና ቅልጥፍናን ለመጨመር በከፍተኛ መጠን እያገለገለ ይገኛል። በኢኮኖሚው ረገድም መረጃዎች እንደሚያሳዩት የእዚህ ቴክኖሎጂ ድርሻ በዓለም ገበያ 350 ቢሊዮን ዶላር በላይ ደርሷል። ይህ ቴክኖሎጂ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን እና ሕይወታችንም ሰፊ ድርሻ እየያዘ መጥቷል።

ያደጉትም ሆነ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ቴክኖሎጂው በሚያስፈልጋቸው ዘርፎች እንደ አስፈላጊነቱ እየተጠቀሙበት ችግሮቻቸውን እየፈቱ ይገኛሉ። ኢትዮጵያም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለሰው ሰራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ነው። የሰው ሰራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂን በመጠቀም የግብርና፣ የጤና፣ የደህንነት እና የመሰል ዘርፎችን አቅም ለማሳደግ እየተሰራ ይገኛል።

ወጣት አብዲዋቅ በቀለ ይባላል። ተወልዶ ያደገው በመዲናችን አዲስ አበባ ከተማ ቤተል አካባቢ ነው። ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ትምህርቱን በአካባቢው በሚገኘው ኦሜጋ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትሏል። በትምህርት አቀባበሉ ጥሩ የነበረው አብዲዋቅ በአስራ ሁለተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ጥሩ ውጤት በመምጣት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱን ለመከታተል በ2009 ዓ.ም ወደ ጅማ ዩኒቨርሲቲ በማቅናት በኮምፒውተርና ኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ በመጀመሪያ ድግሪ ተመርቋል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ በዚሁ የትምህርት ዘርፍ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እየተከታተለ ይገኛል።

ወጣት አብዲዋቅ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የነበረው ቆይታ ምን ይመስል እንደነበር ሲናገር፤ ወደ ጅማ ከተማ ያቀናው በሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቆይታው አብረውት ከነበሩ ጓደኞቹ ጋር ስለነበር ከአካባቢው መቀየር ውጭ በቶሎ ከሁኔታዎች ጋር ለመላመድ አልተቸገረም። ከልጅነቱ ጀምሮ ብዙ ሰዓቱን ኮምፒውተር ላይ ያሳልፍ የነበረው አብዲዋቅ፤ እክል የገጠማቸው የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን በመጠገን መልሶ ወደ አገልግሎት ያስገባ እንደነበር ይናገራል። ጅማ ዩኒቨርሲቲ



ወጣት አብዲዋቅ በቀለ፣

ሲቀላቀልም እንደህልሙ በኮምፒውተር ምህንድስና የትምህርት ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱን በመከታተል በዚህ የቴክኖሎጂ መስክ ለሀገሩ መልካም አበርክቶ ጥሎ ማለፍ እንደሆነ ያስረዳል።

ወጣት አብዲዋቅ እንደሚናገረው፤ ኮምፒ ውተር ኢንጂነሪንግ የሶፍትና ሃርድዌር ሳይንስን በቂ ሊባል በሚችል መልኩ የሚያጠና መሆኑ ለሥራው በከፍተኛ ደረጃ አጋዥ ሆኖለታል። ወጣቱ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር በነበረው ቆይታ ወደ ምርምርና ፈጠራ ሥራው የገባበትን አጋጣሚ ምን ይመስል እንደነበር ሲናገር፤ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪ በነበረበት ወቅት በጅማ ዩኒቨርሲቲ በሚሰጠው የማኅበረሰብ ተኮር የትምህርት ፕሮግራሙ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመሆን የተለያዩ የማኅበረሰቡን ችግሮች ለመፍታት ጥረት ያደርጉ እንደነበር ያስታውሳል።

ወጣቱ ከሁለት ጓደኞቹ ጋር በመሆን የማኅበረሰቡን ችግሮች በመለየት መፍትሔ ለማበጀት ጥረት በሚያደርግበት ወቅት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ መሰረት የሆነውን ግብርና በማስቀደም በዚህ ዘርፍ ያለውን ችግር ለመቅረፍ በሰው ሰራሽ አስተውሎት በመመርኮዝ አንድ የፈጠራ ውጤት ይዞ ብቅ አለ። ይህ ሥራውም የአፈር አይነትን በመመርመር ለየትኛው የሰብል አይነት መሆን ይችላል ወይም ምን አይነት ምርት ቢዘራበት የተሻለ ውጤት ይሰጣል፣ ምን አይነት ማዳበሪያ መጠቀም ይገባል የሚሉ እና በአጠቃላይ አፈሩ ምን ይዘት አለው? የሚሉትን ለመለየት የሚያስችል ለመመርመር የሚያስችል የፈጠራ ሥራ ይዞ ብቅ አለ።

በዚህ ሥራው በቅርቡ ነጋድራስ የሚል ስያሜ ይዞ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በተካሄደው የፈጠራ ሥራ ውድድር ተሳትፎ የሶስተኛ ደረጃን ይዞ በማጠናቀቅ የሶስት መቶ ሺህ ብር የገንዘብ ሽልማት አሸናፊ መሆን ችሏል። በኢትዮጵያ ግብርና ያለው ትልቁ ችግር ምርት ከመዝራት በፊት መሬቱ ምን አይነት ንጥረ ነገር ይዟል የሚለውን በትክክል አለማወቅ ነው የሚለው ባለሙያው፤ በዚህ ቴክኖሎጂ አማካኝነት መሬቱ ያለውን ሀብት ቀድሞ በመለየት ተጨማሪ የሚደረጉ ነገሮች ልካቸው ታውቆ ምርትና ምርታማነትን በሚያሳድግ መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል ይላል።

እንደ ሀገር በተጠና ጥናት በአሁኑ ወቅት በሄክታር የሚገኘው የምርት መጠን እስከ 24 ኩንታል እንደሆነ የሚናገረው አብዲዋቅ፤ ይህንን የምርት መጠን ደግሞ በሄክታር እስከ 49 ኩንታል ማድረስ እንደሚቻል በቅርብ የተሰሩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ የመሬቱ ወይም የአፈሩ ትክክለኛ ምንነት ማወቅ ሲቻል ነው። ለእዚህ ደግሞ ይህ ቴክኖሎጂ ፋይዳው ትልቅ መሆኑን ያስረዳል።

ቴክኖሎጂው እንደ ሀገር ያለው ጠቀሜታ ምን አይነት ነው የሚለውን በተመለከተ የፈጠራ ባለሙያው ሲናገር፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ግብርና እንደመሆኑ በዚህ ዘርፍ የሚደረግ ውጤታማ የፈጠራ ሥራ ችግሮችን በቀላሉ በመፍታት እያንዳንዱ ዜጋ ድረስ የሚዘልቅ ትርጉም ያለው እንደሆነ ይናገራል። ተግባራዊነቱ በተመለከተ ደግሞ፤ ሶፍትዌሩንም ሆነ ሃርድዌሩን በማምረት ለደንበኞች የማቅረብ ሥራ መጀመሩንም ይናገራል፡፡ አፈር ወደ አስራ አንድ የሚደርሱ ባህሪያት (ፎቶታይፖች) phototype ያሉት እንደመሆኑ በግብርና ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች ስለመሬታቸው አፈር ማወቅ ስለሚፈልጉት የትኛውም አይነት ነገር በቂ መረጃ በመስጠት አገልግሎት ላይ እየዋለ እንደሆነ ተነግሯል።

ከሌሎች ጋር ለመወዳደርና በግብርና ቴክኖሎጂ ሃርድዌር ማኑፋክቸሪንግ ላይ በቂ አቅም ለመገንባት የሚሆን የፋይናንስ ችግር ለሥራቸው ትልቅ ማነቆ ሆኖ እንደተጋረጠባቸው የሚናገረው ወጣት አብዲዋቅ፤ ይህንን ግዙፍ ኢንዱስትሪ በተገቢው መልኩ ለማዘመን የመንግሥትም የግልም ተቋማት ድጋፍ ወሳኝነት ያለው በመሆኑ ከጎኑ እንዲቆሙ ይጠይቃል።

በአሁኑ ወቅት (ኦሚሹ ጆይ) የተሰኘ የቴክኖሎጂ ኩባንያ ከጓደኞቹ ጋር በአንድነት መስርቶ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን እየሰራ የሚገኘው የፈጠራ ባለሙያ፤ በዚህ ድርጅት አማካኝነት በሀገሪቱ በተለያዩ ዘርፎች ላይ በማሰማራት የዜጎችን ኑሮ የሚያሻሽሉ ሥራዎችን ለመሥራት ውጥን እንዳለው ተነግሮ፤ ከግብርና በተጨማሪ በጤናና በፋይናንስ ዘርፎች የሚታይ ለውጥ የሚያመጡና እንደ ሀገር ፋይዳቸው ጉልህ የሆኑ የፈጠራ ሥራዎች ይዞ ለመቅረብ ሰፊ እቅድ እንዳለው ገልጿል።

አብዲዋቅ እንደሚናገረው፤ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ማሽን ወይም ኮምፒዩተር የሰው ልጆችን ተክቶ ማመዛዘን፣ መማር፣ ማቀድ እና ፈጠራዎችን ማከናወን እንዲችል የሚያደርግ ነው። በዚህ ሁኔታ ማሽኖቹ አካባቢያቸውን እንዲገነዘቡ፣ የተገነዘቡትን እንዲተነትኑ፤ ችግሮችን እንዲፈቱ ያስችላቸዋል። ይህም በተለይ የሰዎችን ንክኪ በመቀነስ ለምርት መጨመር፣ የጊዜ አጠቃቀምን ለማሻሻል፣ ብልሹ አሰራሮችን ለማስወገድ እና ውስብስብ ስራዎችን ያለ ከፍተኛ ወጪ ለመፈፀም ያስችላል። ከጊዜ አንፃርም ያለማቋረጥ እና ያለ ምንም እረፍት እንደሚሠራ በመጠቆም፤ ይህም የኅብረተሰብን ኑሮ የሀገርን ዕድገት እንደሚያቀላጥፍ ያስረዳል ብሏል።

አሁን ላይ ይህ ቴክኖሎጅ በሁሉም ዘርፎች ሰፊ ተግባራት ያሉት በመሆኑ ከቅንጦት ይልቅ ለኅብረተሰብ ያለው አስፈላጊነት ግንዛቤ እያገኘ እንደመጣ የሚገልጸው ወጣቱ፤ ቴክኖሎጂው ግብርናን በማሳደግ በሀገሪቱ ለሚታየው የምግብ እጥረት መፍትሔ ከማምጣት ባለፈ በተለይ በአፍሪካ በሽታዎችን ለመቀነስ፣ የጤና እንክብካቤን እና ትምህርትን ለማሻሻል፣ ድህነትን ለመቀነስ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያግዝ ይናገራል።

ወጣት አብዲዋቅ እንደሚያስረዳው፤ በሚመጣው ዘመን ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ለቴክኖሎጂ ሥራና ምርምር ትልቅ ትኩረት ያስፈልጋል። ቴክኖሎጂ የተለያዩ ሀገራት የሰው ሰራሽ አስተውሎትን በተመለከተ የተለያዩ ሥራዎችን እየሰሩ ይገኛሉ። በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለመሳብ ጥረት እያደረጉ ነው። ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ መንግሥት የነቃ ተሳትፎ በማድረግ ቴክኖሎጂን ከግምት በማስገባት የፖሊሲ ማሻሻያ በማድረግ ብሎም በቴክኖሎጂ ላይ ለተሰማሩ ተቋማትና ግለሰቦች አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉ የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ መስራት እንዳለበት ያስገነዝባል።

ኢትዮጵያ በዘርፉ ብዙ መስራት የሚችሉ አቅም ያላቸው ወጣቶች አሏት የሚለው አብዲዋቅ፤ ነገር ግን ጉዳዩ የሚመለከታቸውና በቴክኖሎጂ ዘርፍ በተገቢው መንቀሳቀስ ያለባቸው ተቋማት በዛ ልክ እየሰሩ አይደለም። ቢሆንም በዚህ ዘርፍ እየሰራ ያለው ወጣት የሚደግፈኝ አካል የለም ብሎ መንቀሳቀስ ማቆም የለበትም የራሱን ጥረት ማድረግ አለበት ይላል። እዚህ ደረጃ እስኪደርስ ድረስ መንግሥት ወይም አንድ ተቋም የተለየ ድጋፍ እንዳላደረገለትና በራሱ ባደረገው የግል ጥረት እዚህ መድረስ እንደቻለ የሚናገረው አብዲዋቅ፤ ወጣቶች ባላቸው አቅም የሚታይና ተጨባጭ የሆነ ነገር ለመስራት ጥረት ማድረግ እንደሚገባቸው ገልጿል።

ወጣት አብዲዋቅ ባስተላለፈው መልዕክት፤ አንድ ነገር ለማድረግ ሲታሰብ ሁል ጊዜ ዋጋ መክፈል ይኖረዋል፤ ፅንቶና ተግቶ በመስራት ግን የማይሳካ ነገር የለም፡፡ የሀገሪቱን የወደፊት ዘመን መልካም የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ ያለባቸው የእዚህ ትውልድ ወጣቶች ለዓላማቸው መሳካት መክፈል ያለባቸውን መስዋዕትነት ሁሉ መክፈል እንዳለባቸውና፤ የነገው ራዕያቸውን ከግብ ለማድረስ ቀን እና ሌሊት ሳይሉ ተስፋ ባለመቁረጥ መትጋት እንደሚገባቸው አስረድቷል።

በምግብ እራስን ችሎ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የማገዝ ጉዳይ ከልማዳዊ አሠራር ሥርዓት ማላቀቅ የግድ እንደሆነ የሚናገረው አብዲዋቅ፤ ኋላ ቀር አሠራሮችን በመፈተሽ ቴክኖሎጂ ተግባራዊ በማድረግ ዘርፉን ለማዘመን እስትራቴጂካዊ አሰራሮች ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚያስፈልግ ተናግሯል።

ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቅ በኋላ በኢትዮ ቴሌኮም መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ሥራውን የጀመረው አብዲዋቅ፤ ይህንን ጥሩ የሚባል ደሞዝ የሚያስገኘውን ሥራ ትቶ ሕልሙን ለማሳከት ወደ ግል ሥራው ለመስማራት ሲወስን ከጎኑ ሆነው ያበረታቱትን ጓደኞቹንና ቤተሰቦቹን አመስግኗል።

# ለውጦችን እያስመዘገበ ያለው የሲዳማ ክልል የማዕድን ጥናትና ልማት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በቡና፣ በቱሪዝም መስህቦቹና በሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶቹ በስፋት የሚታወቀው የሲዳማ ክልል በርካታ የማዕድን ሀብቶችም አሉት፡፡ በክልሉ ወርቅ፣ የከበሩ ማእድናት፣ ለኮንስትራክሽና ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውሉ በርካታ የማዕድን አይነቶች ይገኛሉ፡፡

ክልሉ በአዲስ ክልልነት በቅርብ ጊዜ የተዋቀረ እንደመሆኑ ቀደም ባሉት ጊዚያት በክልሉ ያሉ የማዕድን ሀብቶችን በመለየት ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ሥራዎች እምብዛም አልተሰሩም፡፡ ከቅርብ ጊዚያት ወዲህ ግን በክልሉ ያሉ ማዕድናትን በጥናት በመለየት ጥቅም ለማዋል ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ እስካሁን በክልሉ ያለውን የማዕድን ሀብት ለማወቅ በተደረገው ጥናት 20 በመቶ ያህሉ የማዕድን ሀብቶችን በጥናት መለየት የተቻለ መሆኑን ከክልሉ የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡

መረጃው አሁን ላይ በክልሉ ያለውን የማዕድን እምቅ ሀብት ለማወቅ የሚያስችሉ ቀጣይነት ያላቸው ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን ያሳያል። የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው የክልሉን የማዕድን ሀብት ልማት አስመልክቶ የሲዳማ ክልል ውሃና ማዕድን ቢሮ የማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ መስፍን መጩካ እንዳሉት፤ በክልሉ ያሉትን ማዕድናት ለመለየት ጥናት እየተካሄደ ነው፡፡ ዘንድሮ ዝናብ በመራዘሙ ምክንያት የማዕድን ልየታ ሥራው የተጀመረው በቅርቡ ነው፡፡ ልየታው በኤጀንሲ በራስ አቅም፣ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲና በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ኢንስቲትዩት ነው የሚካሄደው፡፡ በተለይ በከበሩ ማዕድናት ዙሪያ የሚደረጉት ጥናቶች በራስ አቅምና ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

አሁን ላይ በክልሉ ያሉትን ማዕድናት ለማልማት የሚሰሩ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠላቸውን ዋና ዳይሬክተሩ ያመላክታሉ። በዚህም በበጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት በማዕድን ዘርፉ ለማግኘት ከታቀደው አንጻር የተሻለ አፈጻጸም እንደተመዘገበም ይናገራሉ፡፡

በተያዘው የበጀት ዓመት በስድስት ወራት የወርቅ ማዕድን የማምረት ሥራ 15 ኪሎ ግራም ወርቅ ለማግኘት ታቅዶ፤ አምስት ነጥብ አምስት ኪሎ ግራም ወርቅ ማምረት ተችሏል፡፡ በክልሉ እየተመረተ የሚገኘው ወርቅ የደለል ወርቅ የሚባለው ብቻ ሲሆን፤ የኳርዝ ወርቅ በክልሉ መኖሩ ቢታወቅም ገና ጥናት እየተደረገበት ነው፡፡

በማዕድን ዘርፍ በበጀት ዓመቱ በስድስት ወራት ስድስት ሚሊዮን ብር ገቢ መገኘቱን ዋና ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፤ ከፍተኛው ገቢ ከሮያሊቲ ክፍያ የተገኘ እንደሆነም አመላክተዋል፡፡ በዘርፉ ሥራ አጥ ለሆኑ ሦስት ሺ ሦስት መቶ በላይ ወጣቶች የሥራ እድል እንደተፈጠረላቸውም አስረድተዋል፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚውሉ እንደተልክ፣ ሮታይል እና ካኦሊን ያሉ ከውጭ ሀገር በከፍተኛ ወጪ የሚገቡ ማዕድናትን በሀገር ውስጥ በማምረት ለኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት የማቅረብ ሥራ እየተሰራ ነው፡፡ በስድስት ወራት ውስጥም 120ቶን የኢንዱስትሪ ግብዓት ማዕድናት ለማምረት ታቅዶ፤ 105 ቶን ማዕድናት በማምረት ለኢንዱስትሪዎች ማቅረብ ተችሏል፡፡

‹‹ኅብረተሰቡን በማዕድን ሀብት ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር የየአካባቢውን ማኅበረሰብ ተጠቃሚነት ለማረጋጋጥ የሚያስችሉ የኮንስትራክሽን ማዕድናትም ይመረታሉ ››ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የኮንስትራክሽን ማዕድናት አብዛኛውን ኅብረተሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ

> **የማዕድን ልማት እውቀትን፣ የማልማት አቅምን እንደሚፈልግ ተናግረዋል፡፡ ማዕድኑን ለማውጣት የሚያገለግሉ ማሽኖች እንዲኖራቸው እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል፡፡ በማኅበር ተደራጅተው የሚሰሩት ወጣቶች ያላቸው እውቀት፣ አቅምና ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑ በፍጥነት ወደ ሥራ ለመግባት እንደገደባቸውም አስታውቀዋል**

መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡ በስድስት ወራቱ ከ90 በመቶ በላይ የኮንስትራክሽን ማዕድናት በማምረት ለገበያ የቀረበ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

በክልሉ ያለው የማዕድን ሀብት ገና እየተጠና መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፤ በማዕድን ዘርፉ የተሰማሩ በርካታ ባለሀብቶች ጥናት እያደረጉ መሆናቸውን ጠቁመው፣ አብዛኛዎቹ እስካሁን ወደ ምርት ደረጃ እንዳልደረሱ አመላክተዋል፡፡ በማዕድን ዘርፍ ሰፊ ስራ እየተሰራ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፤ በተለይ በማዕድን ሥራ የተጎዳውን መሬትን መልሶ በማቋቋም ስምንት በመቶ በላይ የሚሆን የተጎዳ መሬት መልሶ እንዲያገግም መደረጉን አስታውቀዋል፡፡

በክልሉ የግራናይት ማዕድን በስፋት መገኘቱ ተረጋግጧል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ በግራናይት ማዕድን ልማት ለመሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶች ፈቃድ ወስደው የምርመራ ሥራ ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል፤ ባለሀብቶቹ የምርመራ ሥራውን ሲያጠናቅቁ ወደ ማምረት ሥራ እንደሚገቡ አስረድተዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ በክልሉ በርካታ የኢንዱስትሪ ማዕድናትንም ይገኛሉ፡፡ እንደ ተልክ ያሉ (ለሴራሚክ ግብዓት የሚውሉ)፣ ኳርዝ፣ ካኦሊን፣ ዶይሎማይት እና ሮታይል በመባል የሚታወቁት እና ሌሎች ማዕድናት በክልሉ የሚለሙ ናቸው፡፡ በተለይ በዚህ ዓመት ‹‹ሮታይል›› የተሰኘውን ማዕድን ማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ማኅበራት እያመረቱ ከፍተኛ ገቢ እያገኙ ነው፡፡ ሌሎችም የኢንዱስትሪ ማዕድናት በጥናት የተለዩ ቢሆንም ግን እስካሁን ወደ ሥራ ያልገቡ አሉ፡፡

በቀጣይ እነዚህን ማዕድናት በሥራ ላይ ለማዋል የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል፡፡ ማዕድናት የማውጣት ሥራው ቀለል ያሉትን ማዕድናት ለማልማት በማኅበር በተደራጁ ወጣቶች የሚሰራ መሆኑን ገልጸው፣ ከበድ ያሉትና በማሽኖች መስራት የሚጠይቁትን በዘርፉ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች እንደሚሰጡ ገልጸዋል፡፡

በክልሉ በማዕድን ልማት ላይ ለመሳተፍ የምርመራ ፈቃድ የወሰዱ በርካታ ባለሀብቶች ያሉ መሆኑን ጠቁመው፤ ፍቃድ ከወሰዱት ውስጥ በግላቸው ሳይሆን ከማኅበራት ጋር በመሆን ያመረቱ ከስድስት በላይ የሚሆኑ ባለሀብቶች መኖራቸውን ያስረዳሉ፡፡

የኮንስትራክሽን ማዕድናት ለማምረት ፈቃድ የወሰዱ በከፍተኛ ደረጃና አነስተኛ ደረጃ ያሉ ብዙ አምራቾች አሉ ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ረገድ በጣም ሰፊ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከኢንዱስትሪ ማዕድናትም አንጻርም እንደ ተልክና ኳርትስ የመሳሰሉት ማምረት የተጀመረ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተያዘው በጀት ዓመት ተጨማሪ ‹‹ሮታየል›› የተሰኘ ማዕድን ማምረት መጀመሩን አስታውቀዋል፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ፤ አሁን ላይ በክልሉ የግራናይት ማዕድን ለማምረት ሁለት ድርጅቶች በሁለት ቦታዎች ላይ የምርመራ ሥራ መጀመራቸውን ይገልጻሉ፡፡ በዘንድሮ ዓመት የግራናይትና የሊትየም ማዕድናት ፈቃዶች የተሰጡ መሆናቸውን የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በግራናይት አምስት ባለሀብቶች እና በሊትየም ሁለት ባለሀብቶች የምርመራ ሥራ እየሰሩ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በክልሉ የማዕድን ማምረት ሥራ የተሰማሩት አካላት ቀደም ሲል በክልሉ ማዕድን ልማት ሥራ ከተሰማሩት ወጣቶች ጋር በመቀናጀት የሽርክና ማኅበር መስርተው እየሰሩ ያሉ ማኅበራት መሆናቸውንም ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ በክልሉ እስካሁን ያለውን ማዕድን ለማወቅ በተደረገው ጥናት 20 በመቶ ያህል የማዕድን ሀብቶችን መለየት ተችሏል፡፡ በተያዘው በጀት ዓመት ይህን 25 በመቶ ለማድረስ እየተሰራ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ 750ካሬ ሜትር መሬት ጥናት ለማድረግ ታቅዷል፡፡ ይህን እቅድ ከግብ ለማድረስ የሚያስችል ጥናት ተጀምሯል፡፡

‹‹ክልሉ እንደ ክልል በቅርቡ የተቋቋመ እንደመሆኑ መጠን ቀደም ሲል በስፋት ጥናቶች ስላልተካሄዱ በክልሉ ያለው የማዕድን ክምችት ብዙም አይታወቅም፤ የተሰሩትም የአለኝታ ጥናቶች ናቸው ››ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህም ደግሞ አሁን ላይ በክልሉ ምን ያህል ማዕድን ሀብት እንደሚገኝ ለማወቅ እንዳላስቻለና የማዕድን ልማቱ ችግር ሆኖ መቆየቱን አንስተዋል። በክልሉ ማዕድን ልማት ለመሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶች በጥናት የተለየ የማዕድን ሀብት ያለበት ቦታ እንደሚፈልጉ ጠቅሰው፤ ይህን ችግር ለመፍታት ኤጀንሲው በማዕድናት ዙሪያ ጥናት እያደረገና ባለሀብቱም በማዕድን ጥናት እንዲሳተፍ የማበረታታት ሥራዎች እየሠራ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በማዕድን ዘርፉ በማኅበራት ተደራጅተው የሚሰሩ ወጣቶች በፍጥነት ወደ ማዕድን ልማት ሥራ አለመሰማራታቸው ዋነኛ ተግዳሮት መሆኑን የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የማዕድን ልማት እውቀትን፣ የማልማት አቅምን እንደሚፈልግ ተናግረዋል፡፡ ማዕድኑን ለማውጣት የሚያገለግሉ ማሽኖች እንዲኖራቸው እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል፡፡ በማኅበር ተደራጅተው የሚሰሩት ወጣቶች ያላቸው እውቀት፣ አቅምና ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑ በፍጥነት ወደ ሥራ ለመግባት እንደገደባቸውም አስታውቀዋል፡፡

የማዕድን ዘርፉ ከሌሎች የሥራ ዘርፎች አንጻር ሲታይ የሥራ እድል በመፍጠርና በፍጥነት ለማደግ የሚያስችል የተሻለ ዘርፍ መሆኑን የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በዘርፉ የአቅም ውስንነት እየታየ መሆኑንም አመላክተዋል፡፡

የዘርፉ ሌላኛው ተግዳሮት ወርቅ በሚመረትበት አካባቢ የሚደረገው ሕገወጥ ዝውውር እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ከሚመረተው የወርቅ ምርት አነስተኛ መሆኑ ጋር ተያይዞ የሚታይ ሰፊ ሕገወጥነት ችግር እንደሌለም ጠቅሰው፣ የጥቁር ገበያ ዋጋ ከፍ ያለ መሆን ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግን እንደሚፈልግ ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል፡፡ ‹‹ክልሉ አዲስ በመሆኑ በዘርፉ ያለው የሰው ኃይል አነስተኛ መሆን እና ከግንዛቤ እጥረት የተነሳ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ አለመቻል ሕገወጥነት እንዲስፋፋ አድርጎል›› ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ በክልሉ ለሚደረገው የማዕድን ጥናት የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ኢንስቲትዩት የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ ነው፡፡ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ክልሉ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ከኤጀንሲ ጋር አብሮን እየሰራ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው በየዓመቱ መስራት የሚገባው ሥራ እየሰራ ኤጀንሲውን እየደገፈና በቅንጅት አብሮ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ በዘንድሮም ዓመትም በባለፈው ዓመትም ያጠናውን ጥናት ለኤጀንሲው ለማስረከብ ዝግጅት እያደረገ ነው፡፡

በማዕድን ዘርፉ በሀገር ደረጃ የተያዙ የትኩረት አቅጣጫዎችን ከግብ ለማድረስ ክልሉ እየሰራ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በአገሪቱ ያላትን ብዙ የማዕድን ሀብቶች በጥናት በመለየት መጠቀም እንዲቻል በክልሉ የሚሰሩ ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አረጋግጠዋል፡፡

‹‹ማዕድን አገራችንን ማሳደግ የሚችል ብዙ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ረገድ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ በተለይ የከበሩ ማዕድናት በማልማትና እሴት ጨምሮ ለውጭ ገበያ በማቅረብ ለሀገር የውጭ ምንዛሪ ለማምጣት ትኩረት ተደርጎ ይሰራል›› ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ እንደ ክልልም አገሪቱ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከውጭ አገራት የምታስገባቸውን ማዕድናት በራስ አቅም በአገር ውስጥ በማምረት መተካት ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ነው›› በማለት ያብራራሉ፡፡

‹‹ማዕድን በክልሉ ያለውን የሥራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ አንዱ ትልቁ አቅም ተብሎ ነው የሚጠበቀው፡፡ ወጣቶችም በዚህ ዘርፍ ሲሰማሩ ቶሎ ማደግ እንዲችሉ የሚያስችል ዘርፍ ነው። ወጣቶች በዘርፉ ላይ እንዲሰማሩና ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ በሥራ አጥነት በመቅረፍ የዳበረ የኢኮኖሚ አቅም እንዲኖራቸው ማስቻል ነው›› በማለት ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል ፡፡

መንግሥት በሀገር በቀል ኢኮኖሚው ትልቅ ትኩረት ከሰጣቸው ዘርፎች የማዕድን ዘርፉ አንዱ መሆኑ ትልቅ እምርታ ነው የሚሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በየደረጃው ያለው አመራር በመተባባር በዘርፉ የሚስተዋለውን ሕገወጥነት በመከላከል ማዕድናት ለሀገር ጥቅም እንዲውሉ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንዳለበት አስገንዝበዋል። ኅብረተሰቡም ከማዕድን ማግኘት የሚገባውን ጥቅም እንዲያገኝ በማድረግ ሀገራችንን ማሳደግ አለብን ሲሉ ገልፀዋል፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ብርሀን

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

በሴትነቷ ፈር ውስጥ የብርሀን ጎርፍ ይንፎለፎላል። በምሽት ጉያዋ ውስጥ የእምዬ ማርያምን ምስል አትማ እንደምትንፏቀቅ ጨረቃ የብርሀን ምንጭ ከቀይ ፊቷ ላይ ይፈልቃል፡፡ ሰው ሆኖ ብርሀናማ መሆን ይቻላል? ሁሌ ከእጄ የማይጠፋው የአፈንጋጩ የኦሾ ፍልስፍና እንኳን የእሷን ውበት ያክል አላስለፈለፈኝም፡፡ ማማር ስትወድ። አንድም ቀን ከላመል ጉድፍ ጋር አላየኋትም።ደም ዘናጭ ናት..ከሰውነቷ ጋር ያበሩ፣ ውበቷን ያጎሉ ደመቅማቃ ልብሶች ታዘወትራለች፡፡

ጸጉሯ አጭር ነው..ፊትሽ ለአጭር ጸጉር የሚሆን ነው ተብላ ረጅም ጸጉሯን ያሳጨደችው ይመስለኛል። ብርሀናማ ፊት ከብርሀናማ አይኖች ጋር ፊት ለፊቴ ሲደነቀሩ አልደነባበርም ለቀን ሙሉ የሚሆነኝን የሀሳብ ስንቅ ከውብ ፊቷ ላይ እቃርማለው፡፡ የሆነ ልማድ አላት..አንድን ሰው ለረጅም ጊዜ የማየት።በዛ አይንና ውበት ለረጅም ጊዜ መታየትን ዳዋውን አስቡት? በውበቷ በኩል ስርየት የሌላቸውን ትላልቅ ሀጢዐቶችን ሰርቻለው። ካህን ፊት ቀርቤ ብናዘዛቸው መዳኛ የማላገኝባቸውን ሀጢዐቶች፡፡ ጸንቼ ሰንብቼ መሰነካከያዬ የእሷ ፊት ነው፡፡

የከፋው ነገር እኔን አትወደኝም፡፡ አንድ ቢሮ ውስጥ ለአስር ስንሰራ የማታወራው ከእኔ ጋር ብቻ ነው፡፡ ዓለም ላይ የሰው ልጅ ሁሉ አልቆ እኔና እሷ ብቻ ብንቀር የምትጎራበተኝ አይመስለኝም፡፡ እኔ ፊትና ሌሎች ወንዶች ፊት ሁለት አይነት ናት፡፡ የምትደናበረውና የምትመናቀረው እኔን ስታይ ነው።አንድ ቀን ቀናኝ..ፊት ለፊቴ ተረከዛማ ጫማዋ ተበጠሰ። በሁለት እጅዋ እንደ እሷ መንገደኛውን የሚያስቀላውጡ መልከኛ ፔስታሎችን አንጠልጥላለች። (እገምታለው ልብስ ነው የያዘችው።በየሳምንቱ ዓርብ በስራ በኩል ገበያ ወጥቶ ያማራትን የመሸመት አመል አላት) ተረከዛማ ጫማዋ ተበጠሰ፡፡ እኔን እርዳታ ከመጠየቅ ውጪ ምንም ምርጫ እንደሌላት በማሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ የምታወራበትን አጋጣሚ በኩፊሳ ስጠብቅ እግሯን እየጎተተች አልፋኝ ሄደች።

እንደዚህ የጠላችኝ ምን በድያት ነው? ወደሚል የሀሳብ አዘቅት ተወረወርኩ፡፡

ከብዙ ቀናት በኋላ አንድ ረፋድ ውስጤ የሚመላለስን ሀሳብ ተከትዬ ከቢሮዬ ወጣሁ። እንደነገሩ ነው የለበስኩት። የመስሪያ ቤታችን እብድ መሳይ ሰራተኛ ነኝ። በዚህ ዝርክርክነቴ እዛች ጣኦት መሳይ ቆንጆ ሴት ፊት ስቀርብ ደፋርነቴ ነው የሚመጣብኝ፡፡ ከአእምሮ እንጂ ለአካል ግድ የለኝም፡፡

ማሰብ እወዳለው፡፡ በሆነ ርዕሰ ጉዳይ ላይ መወያየትና መከራከር የምዝናናበት ተፈጥሮዬ ነው። አንዳንዶች አለባበሴን አይተው በሩቁ የማይረባ ያደርጉኛል፡፡ የተረዱኝ ደግሞ በግድም ለወዳጅነት ይመርጡኛል። እንደ እኔ ነፍሱን በሀሳብ ያከሳ ሰው አላውቅም፡፡ አእምሮ አፍ ቢኖረው በአግባቡ የተጠቀሙብኝ ሰው ብሎ ይኩራራብኝ ነበር፡፡ እኔ ስወጣ ጀምበር ስትገባ ከመንገድ ተገናኘን፡፡ ጸሀያማው ቀዩ ጠይም ደመና ለበሰ፡፡ ወዲያው ማካፋት ጀመረ፡፡ የተረገመ ቀን አልኩ፡፡ እንደ ሀሳቤ ሳይሆን ሲቀር እንዲህ የምለው መርገምት አለ፡፡ ጥሩ ላለበሰ፣ ሀሳባዊ ለሆነ ሰው ጸሀይ ሆነ ደመና ምን ሊበጀው? ከካፊያው ሽሽት ከመስሪያ ቤታችን አቅራቢያ ወደሚገኝ ገብቼበት ወደማላውቅ ካፌ ስተት አልኩ፡፡

ተደላድዬ ሳልቀመጥ እንዲሁም ሀሳቤን ፈር ሳላሲዝ አንዲት ጸጉሯን ቀለም ያጠጣች፣ ደረቷ ላይ የእሾህ አክሊል ያለበትን የእየሱስን ምስል ያተመች ሴት ልትታዘዘኝ ፊቴ ተዘባና ቆመች፡፡ ማንም ከዚህ በፊት እንዲያ ባለ ዝብናኔ አስተናግዶኝ አያውቅም፡፡ በዝብናኔዋ አልተቀየምኳትም ይልቅስ አዲስ ሀሳብ አጋባችብኝ እንጂ፡፡ ‹ወተት አልኩ› ብዙ ሳላለፋት፡፡ ካፌ ገብቼ ከወተት ውጪ የምጠጣው ነገር የለም፡፡ አንዳንድ ወዳጆቼ ሲቀልዱብኝ የእናት ጡት ስላልጠገበ ያንን እየተካ ነው ይሉኛል፡፡ እኔ ምን ገዶኝ..አንድ ለመጨረስ በሚሳቀቁ ቄንጠኛ ወዳጆቼ ፊት ሁለት..ሶስቱን ደርግሜ እመለሳለው፡፡ ከእንስሳ የላም አፍቃሪ ነኝ፡፡ ከሰው ደግሞ የራሴ፡፡ ያቺን የመስሪያ ቤታችን ቆንጆ ዘናጭ ሴት ሁለተኛ ላደርጋት ከራሴ ጋር ምክክር ላይ ነኝ።

ከቡሀቃ መለስ ባለ አንዳች በሚያክል ጥንታዊ ብርጭቆ ትኩስ ወተት መጣልኝ፡፡ በዛ ዘመነኛ ቤት ውስጥ ያን ብርጭቆ መኖሩ ዙሪያ ገባዬን እንድቃኝ አደረገኝ። ቤቱ ባህላዊ ቤት እንደሆነ በተቀመጥኩበት ወንበርና፣ ግድግዳው ላይ በተሰቀሉ አንዳንድ ባህላዊ ጌጦች አረጋገጥኩ፡፡ ትልቁ ብርጭቆ ውስጥ ይመጥነዋል ብዬ ያሰብኩትን ስኳር በስሌት ጨምሮ ወደአፌ አስጠጋሁት፡፡ በአንዲት ቀብራራ ሴት የመጣ ነጭ ወተት..ወደ ሆዴ ሲሰርግ በተለየ እርካታ ነበር። አጠጣጤን እየታዘበች ይሆን እንጃ ላጋሳ ቀና ባልኩበት አስተናጋጇን አይኗን አነጣጥራብኝ አገኘኋት፡፡ ደረቷ ግድም በእሾህ አክሊል እየሱስን ወደ አንድ ጎን አዘንብሎ አየሁት፡፡ ካልጠፉ ቦታ የዓለምን ንጉስ እዛ ቦታ ማኖሯ ፈጣሪ በንፍር ውሀ ሊጠብሰን እያኮበኮበ እንደሆነ እንዲሰማኝ አደረገኝ። በሴት ርቃን ላይ፣ ለዛውም በጡት ሰፈር እየሱስን ተስሎ ሳየው ስምንተኛው ሺ መድረሱን አወኩ፡፡ ‹ከፍቅሯ ነው ከድፍረቷ ያን ማድረጓ? ስል ጥያቄ መጣብኝ፡፡

ከቀይ ዳማ ሸሽት ከጠይምነት መለስ ያለ መሀል ላይ ያለ ስም የሌለው መልክ አላት፡፡ ከውበቷ ሁሉ ቶሎ አይን ውስጥ የሚገባው ጡቷና ቆፍጣናነቷ ነው፡፡ የሀበሻ ቀሚስ ለብሳ ቢሆን ፊቴ የቆመችውና የምትታየኝ እቴጌ ጣይቱ በወጣትነቷ ትሆን ነበር፡፡ ጡቶቿ ለእይታ እንዲመቹ ሆነው መልኩን በሚያሳብቅ ጥቁር ጡት ማሳዣ ተጠፍረዋል። ደረቷን ለሁለት ገምሰው ተነፋፍተው እና አጮልቀው። ከአንዴ ልቀው ለዘላለም እንዲታወሱ በሀጢዐተኛ ሴት መላ ተዘባነዋል፡፡ አማረችኝ፡፡ ከወተቱ ጋር እሷን የሚያሰኝ መስተፋቅር ስታኝ ይሆን? አይቻት የማላውቃትን ሴት በአንድ ጊዜ መከጀሌ ስል አሰብኩ። ከሴት ውበት መድከሚያዬ ጡት ነው፡፡ ትልቅ ጡት ያላት ሴት ሰፊ አለሜ ናት፡፡ ሴት ጡት ከሌላት ሴት አትመስለኝም፡፡ አብሬአት ተጋድሜ እንኳን አምሮቴን ለማውጣት የማውቃቸውን ትልቅ ጡት ያላቸውን ሴቶች በሀሳቤ አምጥቼ ነው የምረካው፡፡ የዚህ ዓለም እድለኛዋ ሴት ትልቅ ጡት ከትልቅ መቀመጫና ከትሁት ልብ ጋር ያላት ናት የሚል ምልከታ አለኝ፡፡

ሂሳብ ልከፍላት በዛውም በደንብ ልረዳት በምልክት ጠራኋትና መጣች፡፡ ስትራመድ ለማንም ዝቅ እንዳትይ ተብላ ያደገች ነው የምትመስለው፡፡ ቆፍጣናነቷ ተጋብቶብኝ ትህትናዬን ነጥቆ ‹ሂሳብ ስንት ነው? ስል ተጀነንኩባት፡፡ ለሰላሳ ብር ወተት ያን ያክል መጀነን..

‹ተከፍሏል› አለችኝ፡፡ በማውቀው ቆፍጣናነቷ፡፡

ምን እንዳስደነገጠኝ እንጃ ተከፍሎልኝ የማያውቅ ይመስል ድንግጥ አልኩ፡፡ ማን አባቱ ነው የከፈለልኝ በሚመስል አካኋን ፊቷ ላይ አንጃበብኩ፡፡ የጠጣሁበትን ባላገር ብርጭቆ አንስታ፣ ያዝረከረኩትን ወተት ጠረጴዛውን አባብሳ ከፊቴ እብስ አለች፡፡ ቁፍጣኔዋ ራሷ የከፈለችልኝ እንደሆነ እንዳስብ አደረገኝ፡፡ ከአይኔ ከመሰወሯ በፊት ‹ማነው የከፈለው? ስል ዘለግ ያለ ድምጼን ወረወርኩላት። ትታኝ ትሄዳለች ብዬ ስፈራ ጣቷን ከገባሁ ጀምሮ ወዳላየሁት ቦታ ቀስራ ወደ ከፈለችልኝ ሴት ጠቆመችኝ፡፡ እኔና ሀሳቤ፣ እኔና ምኞቴ.. ዘላለሜ ሳይቀር እዛ ቦታ የጨው ሀውልት ሆነን የበደንን ይመስለኛል ካልሆነ ለምን መራመድ አቃተኝ? በዛ ቦታ ለክፍለ ዘመናት የቆምኩ ይመስለኛል፡፡ ብርሀናማዋን የመስሪያቤታችንን ሴት እያስተዋልኩ። ፊቷን ለግድግዳው ሰጥታ፣ እጇን ደረቷ ላይ አጣጥፋ በሆነ ሀሳብ ተወስዳለች። የማውቀው ፈገግታዋ የለም። ግድግዳውን እያናገረች መሰለኝ፡፡ ሊስማት ከንፈሯ ስር በደረሰው ግድግዳ ቀናሁ። ግድግዳውን ባረገኝ አልኩ፡፡

አመሰግናለው ሳልላት ወጣሁ..

የያዝኩትን መጽሀፍ ረስቼ ኖሮ በነጋታው ቢሮ አምጥታ ስትሰጠኝ ከፈጣሪ ስጦታ የተበረከተልኝ ነበር የመሰለኝ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ሔይቲን ያስጨነቋት ሦስቱ የወንበዴ መሪዎች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ጠመንጃውን እየነቀነቀ ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠት የሚወደው የቀድሞው የፖሊስ መኮንን፣ በአሜሪካ ውስጥ ታስሮ የቀየው ታራሚና የራፕ ሙዚቀኛ የነበረው ወጣቱ ወንበዴ ሔይቲ ውስጥ ለሥልጣን ፉክክር ላይ ናቸው።

ለወራት በወሮበሎች ጥቃት ሥር የቆየችው ሔይቲ፣ ባለፉት ሳምንታት ነውጡ ተባብሶ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣን ለመልቀቅ ተስማምተዋል።

የሽግግር መንግሥት ለመመሥረት ጥረት ላይ የምትገኘው ሔይቲ ቀጣዩ መሪ መሆን በሚሹ ወንበዴዎች ተወጥራለች።

የ47 ዓመቱ የቀድሞው የፖሊስ መኮንን ጂሚ ሼሪዝዬር /ባርቢኪው/ ሔይቲ ውስጥ ከሚገኙ የወንጀለኛ ቡድን መሪዎች እጅግ አደገኛው ላይሆን ይችላል። ነገር ግን በቅርብ ዓመታት ብቅ ብለው ጡንቻ ካወጡ ወንበዴዎች መካከል አንደኛው ነው።

በሚታወቅበት ጥይት መከላከያ ጃኬቱና በጠባቂዎቹ ታጅቦ ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ መስጠት የሚወደው ባርቢኪው፣ ጂ9 የተሰኘው የወሮበላ ቡድኖች ጥምረት መሪ ነው።

ባርቢኪው ጠቅላይ ሚኒስትር አሪዬል ሄንሪን በግላጭ በመቃወም ይታወቃል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሥልጣን እንዲወርዱ ሲጠይቅ ቆይቷል። የጂ9 መሪው ባርቢኪው ራሱን ለተራው ማኅበረሰብ እንደሚታገል፤ ሥልጣን ላይ ያሉ ኃያላንን የሚጠየፍ አድርጎ ነው የሚቆጥረው።



ነገር ግን በአውሮፓውያኑ 2018 በርካታ ሰዎች የተገደሉበት ጅምላ ጭፍጨፋ በማቀናበር ከመከሰሱ በላይ በ2021 ለተከሰተው የነዳጅ እጥረትም ተጠያቂ ነው።

የጂ9 አባላት የመጠጥ እና ምግብት አቅራቢዎች ላይ የሚያደርሱት ጥቃት የሔይቲን ደሀ ማኅበረሰብ ከደቆሱ ምክንያቶች አንዱ ነው።

ባርቢኪው በዋና ከተማዋ ያሉ አስፈሪ የሚባሉ ወንጀለኛ ቡድኖችን በማጣመር ‘ቪቭ አንሳንም’ [አብሮ መኖር] የተባለ ኅብረት ፈጥሪያለሁ ይላል። በዋና ከተማዋ የሚገኘውን የባሕር በር እና የነዳጅ ማስተላለፊያ መስመር መቆጣጠሩ ጉልበት ሰጥቶታል።

ዓለም አቀፍ የፖሊስ ኃይል ወደ ሔይቲ የሚሰማራ ከሆነ የባርቢኪው ተፅዕኖ እያነሰ ሊመጣ እንደሚችል ተንታኞች ይስማማሉ የ26 ዓመቱ ጆንሰን አንድሬ አሊያም ኢዞ ከባርቢኪው በላይ ጉልበተኛ እንደሆነ ይታመናል።

ኢዞ ከቀድሞው የፖሊስ መኮንን ባርበኪው የሚለየው በሚመራው የወሮበላ ቡድን ውስጥ ከታች ተነስቶ 'ቪላይ ዲ ዳይ' የተሰኘው ቡድን መሪ ለመሆን መቻሉ ነው።

ወጣቱ ወንበዴ በርካታ የራፕ ሙዚቃዎችን የለለቀ ሲሆን፣ ዩቲዩብ ላይ 100 ሺህ ተከታዮች በማፍራቱ ከድርጅቱ ሽልማት ማግኘት ችሏል።

በሙዚቃ ቪድዮዎቹ ከሚታየው ማንነቱ ጀርባ ግን በመድፈር፣ አፈና፣ ዕፅ እና መሣሪያ ዝውውር በተባበሩት መንግሥታት የሚወቀስ ግለሰብ ነው። ወጣቱ የወሮበላ ቡድን መሪ ሰብዓዊ እርዳታ እንዳይደርስ እክል በመፍጠርም ወቀሳ ይደርስበታል።

የሔይቲን የወሮበላ ቡድኖችን ያጠኑ ተንታኞች ኢዞ ከሌሎች ለየት የሚያደርገው በመዲናዋ ፖርት-አው-ፕሪንስ የሚገኙ የባሕር ኃይል መተላፊያዎችን መቆጣጠሩ ነው ይላሉ። ይህም ከሌሎች ቡድኖች ቀድሞ የጦር መሣሪያ ለማመላለስ ዕድሉን ይሰጠዋል ማለት ነው።

የተባበሩት መንግሥታት እንደሚለው ኢዞ የአገሪቱን “ደካማ የፀጥታ ሁኔታ” ተጠቅሞ ከደቡብ አሜሪካ ቀጥታ ከሚገባ የዕፅ ንግድ ገንዘብም እያተረፈ ነው።

ኢዞ ከዋና ከተማዋ ባሻገር 35 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው ሚሬባላይ ከተማን ለመቆጣጠር ባደረገው ሙከራ አምስት አባላቱን ያጣ ሲሆን፣ 30 ሰዎች ደግሞ ተገድለዋል።

ሌላው ሔይቲን ከሚያስጨንቁ የወሮበላ ቡድኖች መሪዎች መካከል አንዱ የሆነው ጋይ ፊሊፕ ልክ እንደ ባርቢኪው የቀድሞው ሥራው የፖሊስ መኮንንነት ነበር።

የ56 ዓመቱ ፊሊፕ እ.አ.አ. 2004 ፕሬዚዳንት በርትራንድ አሪስቲድን ከሥልጣናቸው ለመገልበጥ መፈንቅለ መንግሥት ካካሄዱ ሰዎች መካከል መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።

እ.አ.አ. በ2016 በሔይቲ የሕዝብ ተወካይ ሆኖ ተመርጧል። ነገር ግን ቃለ-መሐላ ሊፈፅም ቀናት ሲቀሩት ዕፅ በማዘዋወር ወንጀል ተከሶ ወደ አሜሪካ ለእስር እንዲሄድ ተደረገ። ፊሊፕ በወቅቱ ቃለ-መሐላ ፈፅሞ ቢሆን ኖሮ ያለመከሰስ መብት ይኖረው ነበር።

የቀድሞው አማፂ ባለፈው ኅዳር ነበር ከአሜሪካ እስሩን አጠናቆ ወደ ሔይቲ የተመለሰው። ይህ ሁኔታ “ነዳጅ ላይ እሣት እንደመጫር” ተደርጎ ይቆጠራል።

ፊሊፕ ወደ ሄይቲ ተመልሶ ጠቅላይ ሚኒስትር ሄንሪ ላይ “አመፅ” የሚቀሰቅስ ቪድዮ ቀርፆ በማኅበራዊ ሚድያ ላይ ለማሰራጨት ጊዜ አልወሰደበትም። ቀጣዩ የሔይቲ ፕሬዚዳንት ለመሆን ያለውን ምኞት በግልፅ ተናግሯል።

በዚህ ግርግር መሐል የሔይቲ ሕዝብ ችግር ላይ ነው። ከሀገሪቱ 11 ሚሊዮን ሕዝብ መካከል አምስት ሚሊዮን ገደማው የረሃብ አደጋ ተጋርጦበታል።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ከዓባይ ግድብ...

ከ5ኛው ገጽ የዞረ

ተጠቃሚነት ድንጋጌ ጋር ይጣረሳሉ ። እናም የተፋሰሱ ሀገራት የጋራ የሆነውን የዓባይ የውሃ ሀብት ለማልማት የግብፅ ፍቃድ አያስፈልጋቸውም፡፡

ምክንያቱም፣ ሱዳንና ግብፅ ዓባይን ለትላልቅ መስኖዎችና የኃይል ማመንጫነት ሲጠቀሙበት በአንጻሩ ሌሎች የራስጌ ተፋሰስ ሀገራት ወንዙን የሚጠቀሙበት ለአነስተኛ ኃይል ማመንጫነት ብቻ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት የጋራ የሆነውን ሀብት በስፋት አልምተው የመጠቀም ፍላጎት ስለሌላቸው ሳይሆን ዓለማቀፍ የፋይናንስ ተቋማት በግብፅ ተፅዕኖ የተነሳ ብድር የመስጠት ፍላጎት ስለሌላቸው ነው ፡፡

በአንጻሩ የተፋሰሱ ሀገራት የሕዝብ ብዛት በከፍተኛ ፍጥነት በመጨመር ላይ መሆኑን ተከትሎ የውሃ፣ የምግብና የኃይል ፍላጎታቸው በእጅጉ እያሻቀበ ነው፡፡ የሚያሳዝነው እነዚህ ፍትሐዊ ያልሆኑ የፋይናንስ ተቋማት ለግብፅ ሲሆን እጃቸው ይፈታል፡፡ በዚህም ጭው ባለ በርሀ ግዙፍ መስኖዎችን፤ ሀገሪቱን ሙሉ በሙሉ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ያደረጉ ትላልቅ የውሃ ኃይል ማመንጫዎችን ገንብተዋል። በስተሰሜን የሱዳንና ግብፅ ድንበር ላይ ግብፅ በዓለማችን ረጅሙን የዓባይ ወንዝ በመገደብ በግዙፍነቱ ከዓለም 3ተኛ የሆነውን የአስዋን ግድብ ገንብተዋል፡፡

ግድቡን ከመጀመሯ በፊት ማለትም በ1954 ግብፅ ከዓለም ባንክ ብድር፣ ከአሜሪካ ደግሞ እርዳታ ለማግኘት ጠይቃ ተስፋ ተሰጧት የነበር ቢሆንም፤ ከእስራኤል ጋር በገባችበት ውዝግብ የተነሳ ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ በዚህ የተከፋችው ግብፅ ወዲያው ፊቷን ወደ ሶቪየት ኅብረት በማዞር ባገኘችው ብድር ግንባታውን ማካሄድ ችላለች። የአስዋን ግድብ 10 ዓመት ከፈጀ ግንባታ በኋላ እአአ በ1970 ተጠናቋል። በጊዜው ግድቡ 90 ሺህ ሱዳናውያን ከማፈናቀሉ ባሻገር በቅርስነት ተከልለው የነበሩ ቦታዎችም በውሃ ተውጠዋል ፡፡

በግድቡ ግንባታ ምክንያት የተፈናቀሉ ሱዳናውያንም ከቀዬአቸው 600 ኪሎ ሜትር ርቀው እንዲሰፍሩ ሲደረግ፤ በግድቡ የተነሳ ከቀዬአቸው የተፈናቀሉ ግብፃውያን ግን 40 ኪሎ ሜትር ብቻ እርቀው እንዲሰፍሩ ተደርጓል። ግብፅ ይህን ግዙፍ ግድብ ስትገነባ ከሱዳን ውጭ ሌሎች ሀገራትን ማማከር አይደለም እወቁልኝ እንኳ አላለችም፡፡ ሱዳንንም ያማከረቻት አስባላት ሳይሆን በዜጎቿ ላይ የምትፈፅመውን ግፍ እንድታውቀው ይመስላል ፡፡

የአስዋን ግድብ 2ሺህ 100 ሜጋ ዋት በማመንጨት ግማሹን የሀገሪቱን የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎት ያሟላ ሲሆን፤ ለከፍተኛ መስኖ ልማትም ውሏል፡፡ በዚህ ረገድ ምንም እንኳን ግብፅ እምቅ የኃይል አማራጭ ቢኖራትም፣ ከውኃ የኃይል ማመንጫዎች ውጭ የመጠቀም ፍላጎት የላትም፡፡ አንዳንድ ምንጮች እንደሚጠቁሙት 4 ነጥብ 4 ቢሊዮን በርሜል የነዳጅ ድፍድፍ ክምችት በምድሯ ቢኖርም በቀን እያመረተች ያለው ከ640ሺህ በርሜል በታች ነው፡፡ የተፈጥሮ ጋዝ ክምችቷ ወደ 2 ነጥብ 2 ትሪሊዮን ኩብ የሚጠጋ ሲሆን፤ እያመረተች ያለው ግን ወደ 60 ቢሊዮን ኩብ የሚጠጋ ብቻ ነው፡፡ በቀን 547 ሺህ 500 በርሜል የተጣራ ነዳጅ ታመርታለች፡፡

**በአሁኑ ሰዓት ግብፅ 3 ነጥብ 76 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ታለማለች፡፡ ከአስዋን ግድብና ከዓባይ ወንዝ ያልተገባ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚነሱ በርካታ ችግሮች እንዳሉ ሆኖ በትነትና በስርገት የተነሳ በየዓመቱ ከ12 እስከ 14 በመቶ የሚደርስ ውሃ ከግድቡና ከመስኖ ቦዮች ይባክናል**

ግብፅ ሰፊ የከርሰ ምድር ውሃ እንዳላትም ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ይህ ሁሉ አማራጭ (ለኃይልም ሆነ ለመስኖ ልማት የሚውል ሀብት) እያላት መላው ስስቷና ቀልቧ ዓባይ ላይ ነው። እሷ የተሻለ አማራጭ ያላት መሆኑን አይኔን ግንባር ያርገው ብላ በየአደባባዩ እየማለች፣ እየተገዘተችና እየካደች፤ ኢትዮጵያ ዝናብን ጨምሮ በርካታ አማራጭ የውሃ ሀብት እያላት ጥቁር ዓባይ ላይ ግድብ የምትገነባው ግብፅን ለማንበርከክና ጂኦ ፖለቲካዊ ሚዛኗን ለመጨመር ነው ስትል በየመድረኩ የአዞ እንባዋን እየረጨች ነው፡፡

ግብፅ የዓባይን የተፈጥሮ ፍሰት በመቀየር በርሀውን ለማልማት 30ሺህ 300 ኪሎ ሜትር የመስኖ ቦዮችን ገንብታለች ፡፡ ከአስዋን ግድብ 300 ኪሎ ሜትር ርቀት ያህል ውሃ በመሳብ ቶሽካ የተባለውን ሰው ሠራሽ ሐይቅ በመገንባት በርሀውን እያለማች ትገኛለች፡፡ በአሁኑ ሰዓት ግብፅ 3 ነጥብ 76 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ታለማለች፡፡ ከአስዋን ግድብና ከዓባይ ወንዝ ያልተገባ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚነሱ በርካታ ችግሮች እንዳሉ ሆኖ፡፡ በትነትና በስርገት የተነሳ በየዓመቱ ከ12 እስከ 14 በመቶ የሚደርስ ውሃ ከግድቡና ከመስኖ ቦዮች ይባክናል፡፡ ለዚህም ለመስኖ ከሚያስፈልገው ውሃ በላይ በመጠቀም ማባከንና ጥራት የሌለው የፍሳሽ መውረጃ በግድቡ ላይ ከሚስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ይጠቀሳሉ ፡፡

ከአሜሪካው የካምፕ ዴቪድ ስምምነት በኋላ የግብፅና የእስራኤል ግንኙነት በመሻሻሉ፤ የወቅቱ የግብፅ ፕሬዚዳንት አንዋር ሳዳት የፍልስጤምና የእየሩሳሌም ችግር የሚፈታ ከሆነ ከዓባይ ወንዝ 365 ሚሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ በየዓመቱ ለእስራኤል ለመስጠት ቃል ገብተው ነበር፡፡ ይህ የጂኦ ፖለቲካ የአሰላለፍ ለውጥ ታዲያ በራስጌ የተፋሰስ ሀገራት ላይ ውስብስብ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ አልቀረም ፡፡

ሌላዋ የግርጌ ተፋሰስና ጎረቤት ሀገር ሱዳንም ግድቦችን ገንብታለች፡፡ ለምሳሌ፣ እአአ በ1926 ሴናርን ለመስኖ፣ በ1936 ጀበል አውሊያ ለኃይል ማመንጫና ለመስኖ ገንብታለች፡፡ በ1950 3ኛውንና 420ሺህ ሄክታር መሬት መስኖ የማልማት አቅም ያለው የሮሴሪስ ግድብን፤ እንዲሁም ከእዚህ በተጨማሪ ሌሎች ግድቦችን ገንብታለች፡፡ በዚህም በመስኖ መልማት ከሚችለው 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር መሬቷ 1ነጥብ 9 ሚሊዮን ሄክታሩን ማልማት ችላለች፡፡

በግብፅና በሱዳን በመስኖ እየለማ ያለ መሬት የዓባይን 86 በመቶ ከምታበረክተው ሀገራችን ጋር ስናስተያየው፣ የኢትዮጵያ እዚህ ግባ የሚባል አለመሆኑ ሊያስቆጨን ይገባል፡፡

እንግዲህ ከፍ ብሎ እንደተመለከትነው በዓባይ የውሃ ሀብት ላይ በብቸኝነት እየተጠቀሙ ያሉት ሁለቱ የግርጌ ተፋሰስ ሀገራት በተለይ ግብፅ ናት። በሌላ በኩል የራስጌ ተፋሰስ ሀገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ የከፋ ድህነት ላይ እንደሚገኙ የተባበሩት መንግሥታት የምግብና የግብርና ድርጅት /ፋኦ/ ይፋ ያደረገው መረጃ ያመለክታል። ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርታቸው እጅግ ዝቅተኛ ከመሆኑ ባሻገር የምግብ ዋስትናቸውን ማረጋገጥ እንዳልቻሉ ፋኦ ያትታል፡፡ ምንም እንኳን በኢትዮጵያ አሁን ላይ ኢኮኖሚያዊ እድገቱና የግብርና ልማት ሥራው እመርታ እየታየበት ቢሆንም፤ ንጽጽራዊ የአጠቃቀም ችግሩ ግን ገሃድ ነው፡፡

ለምሳሌ፣ በተፋሰሱ ሀገራት የሚገኝ አብዛኛው ሕዝብ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ አይደለም። አማካኝ የሀገራቱ ኤሌክትሪክ የማዳረስ ፍጥነት ከ30 በመቶ የተሻገረ አይደለም፡፡ ከ65 በመቶ የሚልቀው ሕዝቧ ለልጆቹ ማጥኛ፣ ለቤተሰቡ ምግብ ማብሰያና ለምሽቱ ብርሀን የሚያገኝበት የኤሌክትሪክ ኃይል የለውም፡፡ በፀሎቱ የማታ እራትና መብራት አታሳጣኝ ማለቱም የዚህ ገላጭ ብሂል ነው፡፡ የውኃ ኃይል ማመንጫ በተለይ በራስጌ የተፋሰስ ሀገራት ለምቶ ጥቅም ላይ ባለመዋሉ በእድገታቸውና በልማታቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ይህ የኃይል እጥረት ዜጎች ፊታቸውን ወደ ከሰልና የማገዶ እንጨት እንዲያዞሩ በማድረጉ ከፍተኛ የደን ጭፍጨፋን ከማስከተሉ ባሻገር የአየር መዛባትንና ብክለትን እያስፋፋ ይገኛል፡፡ ለዚህ ነው በተመጣጣኝ ዋጋ ኃይል ማቅረብ የግድ የሆነው፡፡

የራስጌ ሀገራት ግብርና በዋናነት የዝናብ ጥገኛ ቢሆንም፣ በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአየር ፀባይ ለውጥ የተነሳ በየዓመቱ ሊባል በሚችል ሁኔታ ድርቅ ስለሚከሰት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ፈተና ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ ስለዚህ እንደ መስኖ ያለ አማራጭ የውሃ ሀብቶችን በመጠቀም ምርታማነትን ማሳደግ የሕልውና ጉዳይ ነው፡፡ የናይልን የውሃ ሀብት በፍትሐዊነትና በኃላፊነት የመጠቀም ጉዳይ ከዓመት ዓመት እየገፋ ከመምጣቱ ባሻገር የተግባር እንቅስቃሴ ተጀምሯል ፡፡

ለአብነት፣ ታንዛኒያ ከቪክቶሪያ ሐይቅ 170 ኪሎ ሜትር በተዘረጋ ቧንቧ ውሃ በመውሰድ በሀገሪቱ በከፋ ድህነት የሚታወቀውን ካሃማ የተባለውን አካባቢ በመስኖ ለማልማት እየሠራች ነው፡፡ ሌሎች የራስጌ ተፋሰስ ሀገራትም ከወንዙ ድርሻቸውን በመጠቀም የውሃ ኃይል ማመንጫና የመስኖ ግንባታዎችን በማካሄድ ረሀብንና ድህነትን ለመዋጋት ቆርጠው ተነስተዋል ፡፡

ለዓባይ ወንዝ ውሃ 86 በመቶውን የምታበረክተው ሀገራችን ኢትዮጵያም ታላቁን የሕዳሴ ግድብ የምትገነባው ከከፋ ድህነት ለመውጣትና የተፈጥሮ ሀብቷን የመጠቀም ሉዓላዊ መብቷን ለማረጋገጥ ነው፡፡ የዓባይን የ13ኛ ዓመት የግንባታ ሂደትና ውጤቱን ስናስብም እነዚህን ከበስተጀርባው ያሉ ሐቆች በመገንዘብ ሊሆን ይገባል። የዛሬው ምልከታዬንም፣ በዚህ እልባት አደርግና በቀጣዩና በመጨረሻው ክፍል ደግሞ ካቆምሁበት እቀጥላለሁ።

**ሻሎም ! አሜን ።**

# ስፖርት





## «ኢትዮጵያ ታምርት» የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድር ይካሄዳል

ማህሌት ብዙነህ

በቀጣይ የሚካሄደው የኢትዮጵያ ታምርት የ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ ውድድር ጤናማ ሕብረተሰብን በመፍጠር የአምራች ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ ያለመ መሆኑን የኢንዳስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ታምርት የአስር ኪሎ ሜትር የሩጫ ውድድር ሚያዚያ 13 ቀን 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ እንደሚካሄድ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በትናንትናው እለት በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል፡፡

በመግለጫው ላይ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ታምርት ሀገራዊ ንቅናቄ በ2014 ዓ.ም በይፋ የተጀመረ ሲሆን የአምራች ኢንዱስትሪውን ማነቆ የመፍታት እና ዘላቂ የንግድ ትስስር የመፍጠር ዓላማ ያለው ነው፡፡

ይህንንም ለማጠናከር የ2016 የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ እና የአስር ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድር የሚካሄድ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በመሆኑም ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሩጫ እንደምትታወቀው ሁሉ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ቀዳሚ እንድትሆን የዘርፉ ተዋናዮች አቫራቸውን የሚያስቀምጡበት ዝግጅት ነው ብለዋል፡፡

ውድድሩ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረውን የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ውጤታማ ለማድረግ እና ጤናማ ሕብረተሰብን በመፍጠር የአምራች ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ ያለመ መሆኑንም አቶ ታረቀኝ አስታውቀዋል፡፡

በተጨማሪም የኢትዮጵያን ሩጫ ስፖርት ከማሳደግ ባሻገር ፕሮፌሽናል አትሌቶችን በማሳተፍ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የስፖርት ትጥቆችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነታቸውን በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት፣ በአምራቾችና በሸማቾች መካከል የገበያ ትስስር ለመፍጠር እንደሚረዳም አስረድተዋል፡፡

አቶ ታረቀኝ እንደገለጹት፤ በዘንድሮ የኢትዮጵያ ታምርት 10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ በአጠቃላይ ከ10 ሺህ በላይ ተሳታፊዎች ይካፈላሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በውድድሩ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ለሚወጡ ተወዳዳሪዎችም በሁለቱም ፆታ በቅደም ተከተል የ250 ሺህ ብር፣ 150 ሺህ ብር፣ 100 ሺህ ብር፣ 50 ሺህ ብር እና የ25ሺህ ብር የገንዘብ ሽልማት እንደሚበረከትም አስታውቀዋል።

በክለብ ደረጃም ከ1 እስከ 3 የሚወጡ ተወዳዳሪዎች የ100 ሺህ ብር፣ የ75 ሺህ ብር እና የ50 ሺህ ብር ሽልማት ያገኛሉ ብለዋል።

የኢትዮጵያ ታምርት የ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ ላይ ሁሉም ማኅበረሰብ በመሳተፍ ለኢንዱስትሪው ዘርፍ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደረግ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌደሬሽን የተሳትፎና የውድድር ዳይሬክተር አቶ አስፋው ዳኜ በበኩላቸው ባለፈው ዓመት የተካሄደው የኢትዮጵያ ታምርት የሩጫ ውድድር ስኬታማ እንደነበር አስታውሰው፤ ዘንድሮም የተሻለ ውድድር በተሻለ ሽልማት ለማካሄድ በቂ ዝግጅት መደረጉን አስታውቀዋል፡፡

የዚህ ዓመት የኢትዮጵያ ታምርት የጎዳና ላይ ሩጫ ከነበረበት የ5 ኪሎ ሜትር ወደ 10 ኪሎ ሜትር ሲያድግ በተመሳሳይ ሽልማቱም በሁለቱም ጾታዎች ከ100 ሺ ብር ወደ 250 ሺህ ብር ከፍ ማለቱን አስረድተዋል፡፡

በውድድሩ ዕለትም የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተዋናዮች ድርጅታቸውን በመወከል፤ አጋር ድርጅቶች እና ከ 40 በላይ የአትሌቲክስ ክለቦችና መላው የአትሌቲክሱ ቤተሰቦች የሚሳተፉበት መሆኑን አቶ አስፋው አስታውቀው፤ ሩጫው መነሻውን እና መድረሻውን መስቀል አደባባይ እንደሚያደርግ ገልጸዋል፡፡

ውድድር ከዚህ ቀደም በ2015 ዓ.ም በ5 ኪሎ ሜትር ሩጫ በእንጦጦ ፓርክ መደረጉ ይታወሳል።



በውድድሩ በአጠቃላይ ከ10 ሺህ በላይ ተሳታፊዎች ይካፈላሉ ተብሎ ይጠበቃል፣